# የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርስቲ

## 4ኛ ዓመት የሐዲስ ኪዳን የርቀት ተማሪዎች ሞጁል

አዘጋጅ፡- መ/ር ወ/ትንሣኤ በዛ

2014 ዓ/ም

አዲስ አበባ፣ኢትዮ□ያ

**ክፍል አራት (7ቱ መላእክታትና ራእዮሐንስ)**

1. የጴጥሮስ መልእክት------------------------------------------------ 1ኛ
2. የጴጥሮስ መልእክት ---------------------------------------------- 2ኛ
3. የዮሐንስ መልእክት ---------------------------------------------- 1ኛ
4. የዮሐንስ መልእክት---------------------------------------------- 2ኛ
5. የዮሐንስ መልእክት---------------------------------------------- 3ኛ
6. የያዕቆብ መልእክት -------------------------------------------- 1
7. የይሁዳ መልእክት -------------------------------------------- 1
8. የዮሐንስ ራእይ---------------------------------------------- ናቸው፡፡

እግዚአብሔር በልብ የመከረውን በነቢያት ያናገረውን ለመፈጸም ቃል ሥጋ ሆነ (ዮሐ.1÷14)፤ ሥጋ ሆኖ ሕገ ጠባይዐዊን ሕገ መጽሐፋዊን እየፈጸመ አደገ፤ ሕገ ጠባይዐዊ በየጥቂቱ ማደግና እንጨት እየሠባረ ውኃ እየቀዳ እናት አባትን ማገልግሉ ነው (ሉቃ.2÷51)፡፡ ሕገ መጽሐፋዊ ደግሞ ሕገ ኦሪትን መፈጸሙ ነው (ገላ.4÷5)፡፡በስምንተኛው ቀን ቤተ ግዝረት፣በ፵ኛ ቀን ወደ ቤተ መቅደስ በዓመት ሦስት ጊዜ ለበዓል ወደ ኢየሩሳሌም መሔዱ ሕገ ኦሪት ለመፈጸሙ ማስራጃ ነው፡፡ እንዲህ እያደረገ ሠላሳ ዓመት ሲሞላው በእደ ዮሐንስ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ልጅነቱን ከአብ በመንፈስ ቅዱስ አስመስክሮ ዕለቱን ወደ ገዳም ሄደ (ማቴ 3÷16፣ ማር1÷9)፡፡ በገዳም ፵ መዓልትና ፵ ሌሊት ጾሞ፣ ዲያብሎስን በሦስት አርእስተ ኃጣውእ ማለትም በስስት፣ በትእቢትና በፍቀረ ንዋይ ቢፈትነው ስስትን፣በትዕግሥት፣ ትእቢትን በትሕትና ፍቅረ ንዋይን በጸሊአ ንዋይ ድል ነሥቶ ተመልሷል (ማቴ.4÷1-11)፡፡ ከዚያ በኋላ ምድረ እስራኤል ገብቶ ማስተማር ሲጀምር የእጁን ተአምራት አይተው፣ ትምህርቱንም ሰምተው አምስት ገባያ ያህል ሕዝብ ተከተለው ከእነዚህም መካከል ዐሥራ ሁለት ሐዋርያት፣ ሰባ ሁለት ዐርድእትና ሠላሳ ስድስት ቅዱሳት አንስት በአጠቃላይ መቶ ሃያ ቤተሰብን መርጧል፡፡

እኒህ መቶ ሃያ ቤተሰብ ክርስቶስ በዋለበት እየዋሉ ባዳረበትም እያደሩ ወንጌልን ተምረዋል፡፡ ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው ዓለምን አድኖ ወደ አባቱ ካረገ በኋላም ሑሩ ወመሐሩ ባላቸው መሠረት ዓለምን በአራቱም ማዕዛን ተክፋፍለው ወንጌልን ሰብከዋል፡፡ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ወደ ዓለም ሁሉ ሒዱ ወንጌልን ስበኩ ብሎ ሲልካቸው ሐዋርያት በእጃቸው መጻሕፍትን ይዘው አልወጡም፣ ጌታም ወንጌል በቃል እየታስተማረ በልባቸው ጽላት ጻፈላቸው እንጂ በወረቀት ላይ ጽፎ የሰጣቸው ነገር አልነበረም፡፡ ሐዋርያትም የክርስቶስ የማዳኑን ሥራ በዓይናችን አየን፣ የቃሉንም ትምህርት በጆሮአችን ሰማን ከእርሱም ጋር በላን ጠጣንም በእውነት ወልደ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ አድኖናል አምናችሁ ተጠመቁ ትድናላችሁ እያሉ ምስክርነታቸውን እየሰጡ ብዙዎችን አሳምነው አጠመቁ እንጂ መጻሕፍት አልሰቷቸውም፡፡ ኋላ ግን ወንጌል

ወደልደረሰችበት ለመሔድ ሲነሡ አዳዲሶቹ አማኞች ያስተማራችሁን ወንጌል ጽፋችሁ ስጡን ሲላሉ ጽፈውላቸዋል፤ አንድም በቃል ያለ ይረሰል በጽሑፍ ያለ ይወረሳል የሚለውን ብሒል ይዘው ጌታ ሲያስተምር በጆሮአቸው የሰሙትንና ሲፈጽም በዓይናቸው ያዩትን በእነሱም ላይ መንፈስ ቅዱስ በወረደላቸው ጊዜ የተገለጠላቸውን ምሥጢራት ሁሉ ለአዳዱሶቹ ምእመናን እና በእነሱም እግር ለሚተኩ ሁሉ ጽፈው አሰረክበዋል፡፡ ይህ የመጀመሪያው የሐዋርያት ጽሕፍት ወንጌል ይባለል፡፡

ሐዋርያት በተለያዩ የዓለም ክፍላት ሆነው በሌላ ክፍለ ዓለም ላይ ላሉት ምእምናን ጽፈው የላኩአቸው ትምህርታት መልእክታተ ሐዋርያ ይባላሉ፡፡ ለጽሐፈታቸውም የተለያየ ምክንያቶች ነበሩአቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል የመናፈቃን መነሣትና በምእመናን ላይ ይደረስባቸው የነበሩ ፈተናዎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ሐዋርያትም ሐሰተኞች መምህራን ተነስተው የተለያዩ ኑፋቄዎችን እንደስተማሩ ሲሰሙ በያሉበት ሆነው የማነፈቃንን ትምህርት ስሕተትነት የሚያጋልጥ፣ በአንጻሩም የክርስቶስን ትምህርት እውነትነት የሚያረጋግጥ መልእክታትን ጽፈው ምእመናን ወዳለበት ቦታ ይልኩ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ምእመናን ክርስትና በመቀበላቸው ብቻ ብዙ መከራ ይደርስባቸው ነበረና ለማጽናትና በሃይማኖታቸው እንዲጸኑ ለማበረታት ሐዋርያት መልእክታትን የጻፉበት ሁኔታ አለ፡፡ ከእነዚህ መካከል ሰባቱ መልእክታተ ሐዋርያ ተጠቃሽ ነው፡፡ እነሱም ሁለቱ የቅዱስ ጴትሮስ መልእክታት፣ ሦስቱ የቅዱስ ዮሐንስ መልእከታት የሐዋርያ ያዕቆብና የሐዋርያው ይሁዳ መልእክታት ናቸው፡፡ በዚህም ጽሑፋችን እነዚህን ሰባቱ መልእክታትና የቅዱስ ዮሐንስን ራእይ የምንመለከት ይሆናል፡፡

የሐዋርያት መልእክታቱ አጠቃለይ ይዘታቸው ትምህርት ነው፡፡ ትምህርታቸውም ትምህርተ ሃይማኖት /Doctrine/ ሥነ ምግባር /Moral/ እና ሥርዓተ ቤተክርስቲያን /Lorder of church/ ያካትታል፡፡ በዚህም ጽሑፍ በዋናነት የምንዳስሳቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መልእክታቱን ማን ጻፋቸው፣ መቼ ተጻፉ፣ ለምን ዓላማ ተጻፉ፣ ለእነማን ተጻፉ የሚሉት እንደመንደርደሪያ ካነሣን በኋላ አያይዘን የመልእክታቱን አጠቃላይ ይዘትና አከፋፈላቸውን በዝርዝር የምንመለከት ይሆናል፡፡

## የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ መልእክታት፡-

### መግቢያ

ጴጥሮስ የቀድሞ ስሙ ስምኦን ይባል ነበር (ሉቃ.5÷34)፡፡ ስምኦን ማለት “ሰምአኒ እግዚአብሔር” ማለት እንደሆነ የትርጓሜ መምህራን ይናገራሉ፡፡ በኋላ ግን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስ ብሎ ሰየመው፤ ጴጥሮስ በግሪክ ቋንቋ ሲሆን በአርማይክ ቋንቋ ደግሞ ኬፋ ይባላል፡፡ ትርጓሜውም ዐለት ማለት ነው፡፡ (ማቴ.16÷18፤ ዮሐ.1÷43)፤ የሐዋ.ሥራ 15÷14)፡፡

በአንዳንድ ንባቦችም “ስምኦን ጴጥሮስ” እየተባለ ይጠራል:: (ሉቃ.5÷8፤ ዮሐ.21÷2፡7፡11፤ 2ኛ ጴጥ.1÷1)።

የቅዱስ ጴጥሮስ አባቱ “ዮና” ይባላል (ማቴ.16÷17፣ ዮሐ.21÷16፡17)። ከእርሱም ጋር የክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ እንድርያስ የተባለ ወንድም አለው (ዮሐ.1÷41)። ሚስት እንደነበረችው በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦአል (ማር.1÷30፤ 1ኛ ቆሮ. 9÷5) ስሟ ግን አልተገለጠም፤ አንዳንድ ትውፊቶች ‹‹ጴርጴተዌ›› ትባል እንደነበር ይገልጻሉ። ልጆች ስለመኖሩም የተባለ ነገር የለም።

ቅዱስ ጴጥሮስ ከወንድሙ ከእንድርያስ ጋር ከገሊላ ባሕር በስተሰሜን ዮርዳኖስ አቅራቢያ በምትገኘው “ቤተሳይዳ” ተብላ በምትጠራው ቦታ እንዳደገ ይነገራል (ዮሐ.1÷45)። ይህቺ ከተማ የወላጆቹ አገር ናት። በትዳር ላይ ሳለ ግን ከእንድርያስ ጋር አሳ የማጥመድ ሥራ እየሠራ በቅፍርናሆም ከተማ ይኖር እንደነበር እንገነዘባለን (ማር.1÷21፡29)።

## የቅዱሱ ጴጥሮስ መጠራት፡-

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጴጥሮስና አስቀድሙእንድርያስ ያገኛቸው በገሊላ ባሕር ላይ ዓሣ ሲያጠምዱ ነው። ቀድሙ የተዋወቀው እንድርያስ ሲሆን እንድርያስ “መሢህን አግኝተናል” ብሎ ነግሮት ጴጥሮስን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አመጣው። ኢየሱስ ክርስቶስም ኬፋ (ጴጥሮስ) ትባላለህ ብሎ ሰየመው(ዮሐ.1÷41-43)። ብዙም ሳይቆይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲመላለስ ጴጥሮስና እንድርያስ መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ፣ በስምኦን ጴጥሮስ ታንኳ ውስጥ ሆኖ ለሕዝብ ትምህርት ከሰጠ በኂላ ብዙ ዓሣ እንዲያጠምዱ አደረጋቸው። ጴጥሮስ “ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ተለይ” ብሎት ነበር ክርስቶስ ግን አትፍራ “ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ” ብሎ ጠራው፤ ያን ጊዜም ሁሉን ትቶ ተከተለው (ማቴ.4÷18-22) ማር.1÷16-20፣ ሉቃ. 5÷11)።

## የቅዱስ ጴጥሮስ የአገልግሎት ሕይወት፡-

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ከምድረ ፍልስጥኤም ውስጥ በአንጾኪያ ተገኝቶ እንደነበር ተመዝግቦአል። (ገላ.2÷11-14)። ያን ጊዜ ግን ከአሕዛብ ጋር ሲበላ ቆይቶ የተገረዙ ሰዎች በመጡ ጊዜ እነርሱን ፈርቶ ስላፈገፈገና ከአሕዛብ ስለተለየ ጳውሎስ ፊት ለፊት ተቃወመው። ከዚህም ሌላ በመጽሐፈ ስንክሳር ከዮሐንስ ጋር ሆነው በአንጾኪያ ውስጥ ብዙ መከራን እየተቀበሉና ተአምራትን እያደረጉ ወንጌልን እንዳስተማሩ ተመዝግቦአል። በተጨማሪም መጽሐፈ ስንክሳር ቅዱስ ጴጥሮስ ትያጥሮን በተባ ለች አገር አንቀጸ ብጹአን የተባለውን የጌታን ትምህርት እንዳስተማረና ከ70 ዓመት ጀምሮ ጋኔን ያደረበትን ሰው አንደፈወሰ ገልጦ ብዙዎች ሰዎችን በተለይም አገረ ገዢው ቀውስጦስንና ሚስቱ አኩሬስያን በክርስቶስ እንዳሳመነ ይገልጣል።

በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ጴጥሮስ በተደጋጋሚ ተነሥቶአል ምእመናን በተለያዩ ወቅትም ከመካከላቸው እኔ የኬፋ ነኝ ያሉ ነበር። ይህም ሁኔታ ጴጥሮስ በቆሮንቶስ አስተምሮ እንደነበር ያሳያል ብለው የገመቱ ሰዎች አሉ። አንዳንድ የታሪክ ፀሐፊዎች በ1ኛ ጴጥ.5÷13 ላይ በባቢሎን እንደነበር ሆኖ መጻፉን ይዘው በዳንኤልና በሕዝቅኤል ጊዜ ተማርከው በሚጠት ላልተመለሱ ይሁዳዎች ወንጌል አስተምሮ ነበር ይላሉ። ሌሎች ብዙዎች ሊቃውንት ደግሞ እዚህ ላይ ባቢሎን የተባለችው ሮም እንደሆነች ያምናሉ። ቅዱስ ጴጥሮስ በሮም ወንጌል እንዳስተማረ በቤተክርስቲያናችን ታሪክ የታመነ ነው። አንዳንዶች ግን ለ25 ዓመታት ያህል በሮም አስተምሮአል የሚሉት በቤተ ክርስቲያናችን አይታወቅም።

### የቅዱስ ዕረፍት፡-

የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ እንደሚያስረዳው ቅዱስ ጴጥሮስ ሊገደል በተፈለገ ጊዜ ከሮም እንዲወጣ ምእመናን መከሩት። ከሮም በመውጣት ላይ ሳለ ጌታችን መስቀል ተሸክሞ ወደ ሮም ሲሔድ ታየው። አንተ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለህምን? አለው ጌታም አዎን  አለው። በዚህን ጊዜ ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም እንደተሰቀልክ ዳግመኛ በሮም ልትሰቀል ነውን? ብሎ ቢጠይቀው ጌታም አንተም ፈራህ ምን ላድርግ አለው በዚህ ልቡ ተነክቶ ተመልሶ በሰማዕትነት ሞቶአል።

ቅዱስ ጴጥሮስ በሰማዕትነት ያረፈው በኔሮን ቄሣር ዘመን 54-68 ዓ.ም ነው። ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር በአንድ ቀን እንደሆነና ቀኑም ሐምሌ 5 ቀን 68 ዓ.ም እንደሆነ ተመዝግቦአል፡ ሌሎች ሊቃውንት ደግሞ በአንድ ቀን ይሁን እንጂ የተሰውት በአንድ ዓመት አይደለም ይላሉ። አውሳብዬስና ሌሎችም የቤተክርስቲያን ታሪክ ፀሐፊዎች እንዳስረዱት ቅዱስ ጴጥሮስ በስቅላት እንዲሞተ ሲፈርድበት እንደ ጌታዬ ወደ ላይ ልሰቀል አይገባኝም ነገር ግን ቁልቁል ዘቅዝቃችሁ ስቀሉኝ ብሎ ጠይቆአቸው ተዘቅዝቆ ተሰቅሎአል። መጽሐፈ ስንክሳርና ገድለ  ሐዋርያትም ይህንኑ ያስረዳሉ (ስንክሳር ሐምሌ 5)። ጴጥሮስ በስቅለት የሞተበት ቦታ ሲርኪስ አደባባይ ተብሎ ይጠራል። ቅዱስ ጴጥሮስ ሁለት መልእክታትን ጽሮልን አልፎአል። እነዚህንም መልእክታት እያንዳንዳቸው ቀጥሎ እናጠናለን።

### መጀመሪያይቱ የጴጥሮስ መልእክት

### መልእክቱ የተጻፈላቸው ሰዎች

የመጀመሪያይቱ የሐዋርያው የጴጥሮስ መልእክት የተጻፈላቸው ሰዎች ቅዱስ ጴጥሮስ የመጀመሪያይቱን መልእክት የጻፈላቸው ሰዎች በም1÷1 ገልጦአቸዋል፤ እነርሱም በጳንጦስና በገላትያ በቀጰዶትያም፣ በእስያም፣ በቢታንያም የተበተኑ መፃተኞች ናቸው። እነዚህን ሰዎች “ኅሩያን (የተመረጡ)” ብሎ ስለሚጠራቸው አማኞች ክርስቲያኖች) ናቸው። እነዚህ አምስት አገሮች

በታናሽ እስያ ውስጥ የሚገኙ አውራ ጃዎት ናቸው። የመልእክቱ ተቀባዮች የሆኑት በእነዚህ አገሮች የሚገኙት ምእመናን “የተበተኑ መፃተኞች” ተብለዋል።

በቤተ ክርስቲያናችን ያለው የ1ኛ ጴጥሮስ ትርጓሜ እነዚህ ሰዎች በጴጥሮስ በስብከተ ቃሉ ያመኑ በሞተ እስጢፋኖስ የተበተኑ ሰዎች መሆናቸውን ይገልጣል። (ስብከተ ሐዲሳት ገጽ 197) 8ሺ ማኅበረ እስጢፋኖስ የሆኑት ደግሞ በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት መሆኑ ከግብረ ሐዋርያት መረዳት ይቻላል። (የሐዋ.ሥራ 2÷41፣ 4÷4)። ስለዚህ እነዚህ ክርስቲያኖች ያመኑት ቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ነው። በኋላ ደግሞ በቅዱስ ጳውሎስ አገልግሎት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ወንጌል እንደተሰበከላቸው መገንዘብ ይቻላል። እንዲያውም ራሱ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደመሰከረው ጳውሎስ ቀደም ሲል ለእነዚህ ሰዎች መልእክትን ጽፎላቸው ነበር። (2ኛ ጴጥ.3÷15)። የጳውሎስም የስብከተ ወንጌል አገልግሎት የደረሳቸው አማኞች መሆናቸውን በዚህ እንረዳለን። ከመልእክቲቱ እንደምንረዳው እነዚህ አማኞች ቀድሞ በአሕዛብ ፈቃድም ይመላለሱ የነበሩ፤ ሲሆን አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ሆነዋል ምሕረቱንም አግኝተዋል። (2÷9፡10፤ 4÷4)። መልእክቲቱ በተጻፈችበት ወቅት በልዩ ልዩ ፈተናና በመከራ ውስጥ ነበሩ። (1÷6፤ 4÷12)። ለእነዚህ ሰዎች ቅዱስ ጴጥሮስ ይህቺን መልእክት ጻፈላቸው። (1÷1)። የጻፈውም ቀደም ሲል የጳውሎስ ተከታይ ነበረው በዚህ ጊዜ ግን ከጴጥሮስ ጋር ባለው የታመነ ወንድም በሆነው በስልዋኖስ (ሲላስ) እጅ ነው። (5÷12)።

**የተጻፈበት ቦታ፡-**

ቅዱስ ጴጥሮስ ይህቺን መልእክት የጻፈበት ቦታው ‹‹ባቢሎን›› መሆኑን ከራሷ ከመልእክቲቱ መረዳት ይቻላል። ይህንንም መረዳት የሚቻለው ‹‹ከእናንተ ጋር ተመርጣ በባቢሎን ያለች ቤተክርስቲያን ልጄም ማርቆስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።›› ብሎ ከጻፈው ቃል ነው። (5÷13)። ስለዚህ ጴጥሮስ ያን ጊዜ በባቢሎን ነበር ማለት ነው። ለመሆኑ ባቢሎን የተባለችው አገር የትኛዋ ናት? ለሚለውም አንደኛው በፋርስ አጠገብ ያለችው ታላቋ ባቢሎን ናት የሚሉ አሉ። ይህን የሚሉ ወገኖች ቅዱስ ጴጥሮስ በባቢሎን ውስጥ ጳርቴ በተባለች ሀገር በምትገኝ ሚስፖታሚያ አውራጃ ምርኮ ላይ ሳለ መልእክቱን ጽፎ ይሆናል የሚል ግምት አላቸው።

ሁለተኛው ባቢሎን የተባለችው ሮም ናት የሚሉ ወገኖች አሉ። ሮም ለምን ባቢሎን ተባለች ለሚለውም በዚያ ዘመን ሮም ልዩ፣ ልዩ ኃጢአት ይሠራባት ነበርና በግብሯ ባቢሎንን ስለ መሰለቻት ባቢሎን ተብላለች የሚል ነው።

ሦስተኛው ደግሞ ‹‹ባቢሎን ዘግብጽ›› ይሉታል።የቤተ ክርስቲያናችን ትርጓሜው ለምን ባቢሎን ዘግብጽ እንደተባለች ሲተርኩ ‹‹ባቢሎን ዘፋርስ›› አለችና ከዚያ ሲለይ ዘግብጽ አለ። ነጋድያን አልፍው ሲሔዱ ለምለም ቦታ አይተው ይህቺን ባቢሎንን ትመስላለች ስላሉ ባቢሎን ዘግብጽ

ትባላለች፡፡ አንድም ናቡከደነፆር ግብጽ ወርዶ ፈርኦን ኒካዑን ወግቶ ሦስት ዓመት ኑሮ ግብጽ ዘባቢሎን አሰኝቷት ተመልሷልና ባቢሎን ዘግብጽ አለ፡፡ አንድም ባቢሎን ማለት ዝርወት ማለት ነው በግብጽ በዝርውት ያለች ሲል ነው›› (5÷13 ትርጓሜ)፡፡

## የተጻፈበት ዘመን

መጀመሪያይቱ የጴጥሮስ መልእክት ስለተጻፈችበት ዘመን የሚያስረዳ ታሪክ ብዙ አልተገኘም፡፡ አንዳንድ ሊቃውንት ግን ከመልእክቲቱ ይዞታ ለመረዳት የበኩላቸውን ሐሳብ ሰጥተዋል፡፡ ይኸውም መልእክቲቱ የተጻፈችው በመከራ ውስጥ ላሉ ክርስቲያኖች ነው፡፡ መከራው ደግሞ ኔሮን ቄሣር ሮም ከተማ መቃጠል ተጠያቂዎች ክርስቲያኖች ናቸው፣ ብሎ በሐሰት ክርስቲያኖችን ወንጀል ባወጀው ስደት ምክንያት የመጣ መከራ ነው፡፡ ማርቆስና ስልዋኖስም ከጴጥሮስ ጋር የነበሩበት ጊዜ ነው፡፡ ስለዚህ ጴጥሮስ በሮም ከመታሰሩ በፊት 67 ወይም በ68 ዓ.ም ገደማ መሆኑን ያስረዳል፡፡ መልእክቲቱን ስለጻፈበት ቦታና ስለወሰዱለት ሰዎች በትርጓሜው መግቢያ ላይ የተገለጠው ታሪክ እንዲህ ይላል "የጻፈበት አገር ግብጽ ክታብ ወሳጅ የለም (አንድም) አልሚናስ ጳውሎስ አልምጳስ ጳውሎስ ናቸው" ነገር ግን ስለ ሁለት ክታብ ወሳጆች ማንነት የተገለጠ ምንም ነገር የለም፡፡

## መልእክቱ የተጻፈችበት ዓለማ

ቅዱስ ጴጥሮስ ይህቺን መልእክት የጻፈበት በሁለት ዋና ዋና ዓላመ ሲሆን እነሱም፡-

1ኛ. የመልእክቲቱ ተቀባዮች በልዩ ልዩ ፈተና አዝነው ነመበረና ለጥቂት ጊዜ መከራ ቢቀበሉም ቅሉ ወደ ፊት ታላቅ ክብርና ጸጋ እንደሚያገኙበት በማስገንዘብ ሊያጽናናቸው ጽፎታል (2÷20፤ 4÷12-14፤ 5÷10-12)፡፡

2ኛ. በአሕዛብ መካከል ሲመላለሱ ከቀድሞ ሥራቸው ተለይተው ኑሮአቸው መልካም እንዲሆን ሊመክራቸው ጽፎላቸዋል(2÷12) 3÷15፡16፤ 4÷3-6)::

## የመልእክቱ አጠቃላይ ይዘት

መጀመሪያይቱየጴጥሮስ መልእክት የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ትምህርት የያዘች ናት፡፡ (3÷1-7)፡፡ በአጠቃላይ ከክፉ ርቀው መልካም እንዲያደርጉ በጐ የሆነውን ነገር በማድረግ እንዲቀኑ ይጽፍላቸዋል፡፡ (3÷8-14)፡፡ ስለ አገልግሎትም እንደተሰጣቸው ልዩልዩ የእግዚአብሔር ጸጋ መጠን እንዲያገለግሉ ትምህርት ይሰጣል፡፡ (4÷10-11)፡፡ ለሽማግሌዎች (ቀሳውስት) ደግሞ በእረኝነት አገልግሎታቸው ጊዜ ለመንጋው ምሳሌ እንዲሆኑ እንጂ ማኅበሮቻቸውን በኃይል እንዳይገዙ ምክር ያስተላልፋል፡፡ (5÷1-4)፡፡ ለጐበዞች ትህትና እንዲኖራቸው ስለ ትህትና ያስተምራል፡፡ (5÷5፡6)፡፡

በመጨረሻም ክርስቲያኖች ባላጋራቸው ዲያብሎስን በእምነት ፀንተው እንዲቃወሙት ካሳሰበ በኋላ ፍፁማን እንደሚያደርጋቸውና እንደሚያበረታቸው ይገልጽላቸዋል፡፡ (5÷8-11)፡፡

**አከፋፈል**

የመጀመሪያው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት አምስት ምዕራፎች አሉት፡፡ የሚከፈለውም በአምስት ክፍሎች ሲሆን እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፡-

1.መግቢያ (1÷1-2)

- ላኪው ሐዋርየው ቅዱስ ጴጥሮስ ስለመሆኑና ስለተቀባዮቹም ጥቂት ይናገራል (1÷1)
- የላኪው የሀዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሰላምታም በዚሁ ክፍል ይገኛል (1÷2)

2. ስለ መዳን የጻፈላቸው ትምህርት (1÷3-25)

- በልዩ ልዩ ፈተና ቢያዝኑም በነፍሳቸው መዳን ክብር የሞላበት ደስታ እንደሚያገኙ እንድም ለጥቂት ጊዜ በሥጋ መከራ ቢጸናባቸውም ኋላ ፍጹም ተድላ /ተድላ ነፍስ/ እነደሚጠብቃቸው በመናገር ያጽናናቸዋል (1÷3-9)
- ነቢያት ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ ይመራመሩ እንደነበር ይተርካል (1÷10-12)፡፡
- ይህን መዳን ለማግኘት አማኞች ሊኖሩት የሚገባ የቅድስና ኑሮ አንድ በነገረ ድኅነት ጉዞ ላይ የምእመናን ተሳቶፍ ምን እንደሆነ ያብራራል (1÷13-25)፡፡

3. በአሕዛብ መካከል ሲኖሩ ሊያሳዩት ስለሚገባ መልካም ኑሮ (2÷1-3)

- ሊያስወግዷቸውና ሊያደርጉአቸው የሚገቡ ነገሮች (2÷1-3)
- ወደ ሕያው ድንጋይ ወደ ክርስቶስ እንዲቀርቡ (2÷4-8)
- የቀድሞውንና የአሁኑን ሕይወት እያነጻጸረ ከሥጋዊ ምኞች ርቀው መልካም እንዲሠሩ የጻፈው ትምህርት (2÷9-12)
- ስለጌታ ብሎ ለሰው ሥርዐት ሁሉ መገዛት እንደሚገባቸው፤ ማለትም ለነገሥታት፣ ለመኳንንትበአጠቃላይ ለባለሥልጣናት ሕግና ሥራዐት በመገዛት ትሕትናን፣ መታዘዝን፣ ፍቅርንና ሰላምን በማሳየት ለሰዎች መልካም ምሳሌ እንዲሆኑ ይመክራል (2÷13-25)፡፡
- ስለ ጋብቻ የጻፈላቸው ትምህርት፤ ማለትም ሚስት ለባሏ እንድትታዘዝ፣ ባልም ሚስቱን በነገር ሁሉ እንዲያገዛትና፣ በአጠቃላይ አብረው ሰማያዊ መንግሥት ለመውረስ በጽድቅ ሥራ እንዲተባበሩ ያስተምራል፣ ስለመልካም ባል አብርሃምን ስለመልካም ሚስትንትም ሣራን ምሳሌ አድርጎ አንሥቷል (3÷1-7)፡፡
- በጐ ለማድረግ እንዲቀኑ (3÷8-22)

4. በሚቀበሉት መካራ ተስፋ ሳይቆርጡ ቢጸኑ የማያልፍ ተድላና ክብር እንደሚያገኙበት (4÷1-5)

- የክርስቶስን መከራ እያሰቡ የአሕዛብን ፈቃድ ትተው የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያደርጉ አንድም የአሕዛብን ፈቃድ፣ ዝሙት ርክሰት፣ ጠኦት ማምለክ፣ መዳራት ስካር ወዘተ እየፈጸሙ በሳለፉበት ዘመን ፈንታ ቀሪ ዘመናቸውን ለክርስቶስ ፈቃድ እንዲገዙ ይመክራቸዋል (4÷1-11)
- በሚደርስባቸው መከራ ሳይደነግጡና ተስፋ ሳይቆቀርጡ ወደ ፊት ክርስቶስ ሲገለጥ የሚጠብቃቸውን ክብር እያሰቡ ደስ እንዲላቸውና ሐሤት እንዲያደርጉ (4÷12-14)
- መከራ መቀበል ያለባቸው በክፉ ሥራ ሳይሆን፤ በክርስትና ምክንያት መሆን እንዳለበት በክፉ ሥራችን ምክንያት መከራ ብንቀበል ቅጣት መሆኑን፣ በሃይማኖታችንና በመለክም ምግባራችን ምክንያት መከራ ብንቀበል ደግሞ ጸጋ የምናገኝበት አንድም የጽድቅ አክሊል የምንሸለምብት መሆን ያስተምራል(4÷15-19)፡፡
- ሽማግሌዎች በአገልግሎታቸው የሚያገኙት ክብር (5÷1-5)
- ከዚህ አያይዞ በእንተ አትሕቶርእስ፡- እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን እንደሚአዋርድ እራሳቸውን ዝቅ የሚአደርጉትን እንደሚወድ አስተምሯል (5÷5) በትሕትና የሚኖር' ለጥቂት ጊዜ መከራ ውስጥ ያሉ ምእመናን ከጌታ ስለሚያገኙት ጸጋና ክብር (5÷5-11)

5. ማጠቃለያ (5÷12-14)

በመጨረሻም እርስ በእርሳችሁ ተፋቀሩ፣ በክርስቶስ ላመናችሁት ለሁላችሁም ሰላም ይድረሳችሁ ብሎ የአባትነቱን ቡራኬ ሰጥቶ መልእክቱን ካጠናቀቀ በኋላ በስልዋኖስ እጅ ልኰላቸዋል (5÷12፡13፡14)

**ሁለተኛይቱ የጴጥሮስ መልእክት**

**የተጻፈላቸው ሰዎች ፡-**

ሁለተኛይቱ የጴጥሮስ መልእክት የተጻፈላቸው ሰዎች፣ "በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የክብር እምነትን ያገኙ" ተብለው ተገልጠዋል፡፡ (1÷1)፡፡ እነዚህ ምእመናን የመጀመሪያይቱ መልእክት የተጻፈላቸው ምእመናን እንደሆኑ በምዕ 3÷1 ላይ ‹‹ወላጆች ሆይ አሁን የምጽፍላችሁ መልእክቲቱ ይህቺ ሁለተኛይቱ ናት በሚለው ላይ መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህን ምእመናን ከቅዱስ ጴጥሮስ በተጨማሪ ሌሎች ሐዋርያትም ያስተማሩአቸው መሆኑን (3÷2) ላይ ተጠቁሟል፡፡

ይህቺ መልእክት ቅዱስ ጴጥሮስ እንደጻፋት የሚያስረዱ ሁለት መረጃዎች አሉ፡፡

1. በመጀመሪያው ላይ ላኪው "የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ስምኦን ጴጥሮስ" ተብሎ በግልጽ ተነግሮአል፡፡ (1÷1)፡፡

2. ጸሐፊው በቅዱስ ተራራ  የጌታን ክብር ያየና "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" የሚለውን  የአብን ድምፅ የሰማ ሰው መሆኑ ስለተገለጠ ጴጥሮስ መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ (1÷17-18) ጴጥሮስ ይህቺን መልእክት በሚጽፍላቸው ጊዜ በተቀባዮቹ መካከል ሐሰተኞች አስተማሪዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን  የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ሠራዒ፣ መጋቢ የለም ብለው አስተምረዋል፡፡ ይኸም ማለት ለጻድቅ ዋጋ፣ ለኃጥእ ፍዳ የሚሰጥ እግዚአብሔር የለም ፍጥረት ሁሉ በልማድ ይኖራል ማለት ነው፡፡
2. ትንሣኤሙታን የለም ብለው አስተምረዋል፡፡ ትንሣኤሙታን የለም ማለት በሞት ጊዜ ነፍስ ትጠፋለች፣ ሥጋም በመቃብር ፈርሶ በስብሶ ይቀራል እንጅ ሥጋነፍስ ከተለያዩ በኋላ እነደገና ተዋሕደው ተነሥተው ደገ ሥራ የሰሩት እንደመላእከተ በደስታ፣ ክፉ ሥራ የሠሩት ግን እንደ አጋንንት በስቃይ መኖር የለም ማለት ነው፡፡
3. ህልፈተሰማይ ወምድር የለም ብለው አስተምረዋል ይኸ ማለት ትውልድ ያልፋል፣ ትውልድ ይተካል ሰማይና ምድር ግን ለዘለዓለም ይኖራሉ እንጅ ማለፍ የለባቸውም ማለት ነው፡፡
4. አንድ ጊዜ ካመኑና ከተጠመቁ በኋላ ምግባር አያስፈልግም ብለው አስተምረዋል፡፡ ምግባር አያስፈልግም ማለት አምኖ የተጠመቀ ሰው ኃጢአትም ቢሠራ አይኰነንም የመጀመሪያ ሃይማኖቱና ጥምቀቱ ያድነዋል ማለት ነው፡፡

**መልእክቱ የተፃፈበት ዋና ዋና ዓላማዎች፡-**

1ኛ. ከፍ ብለን እንደተመለከትነው የተለያዩ ኑፋቄዎችን አሾልከው የሚያገቡ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ተነስተው ነበረና ምእመናን ከእነዚህ ኑፋቄዎች ራሳቸውን እንዲጠብቁ ለማስጠንቀቅ ነው (2÷1፤ 3÷3)፡፡

2ኛ. የመልእክቲቱ ተቀባዮች ምን እንኳ ስለ ክርስትና ያወቁና በእምናታቸውም የፀኑ ቢሆኑም ከፊት ይልቅ እንዲተጉ አጽንኦት ለመስጠት ጽፎላቸዋል፡፡ (1÷10-15፤ 3÷1-2)፡፡

**የተጻፈችበት ቦታና ዘመን**

ቅዱስ ጴጥሮስ ይህቺን መልእክት ሲጽፍ የሚሞትበት ቀን እንደቀረበ ያወቀው መሆኑን ገልጦአል (1÷13-15)፡፡ የሞተው ደግሞ በሮም ከተማ በ68 ዓ.ም ገደማ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ስለዚህ ይህቺ መልእክት የተፃፈችው ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ በሮም ከተማ በ68 ዓ.ም እንደሆነ ይታመናል፡፡

**የመልእክቱ አጠቃላይ ይዘት**

ሁለተኛይቱ የጴጥሮስ መልእክት የያዘችውን የምግባርና የሃይማኖት ትምህርት ነው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ በዚህ መልእክት መጀመሪያ ሃይማኖትንና በጐነትን፣ ዕውቀትንና ምኞት ማሸነፍን፣ ትዕግሥትንና አምልኰትን፣ ባልንጀራን መውደድንና ፍቅርን አጽንተው ቢይዙ የክርስቶስ የአምላክነቱ ባሕርይ ተካፋዮች መሆናቸውን ገልጦ ይነግራቸዋል (1÷4-7)፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እኛ የእግዚአብሔር ወገኖች ነን ብሎ ተናግሮ ነበር ቅድስ ጴጠሮስም የክርስቶስ የአምላክነቱ ባሕርይ ተካፋዮች ናችሁ ብሎ አስተማሯል (የሐዋ.16፡28-29)፡፡ ስለዚህ በክርስቶስ ያመኑ ምእመናን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን አንድነትና ዝምድና መዓርጋቸውንም ለማክበር ሲሉ ከክፉ ሥራ መጠበቅ እንደሚገባቸው አስተምሯል፡፡ ከዚህ አያይዞ በሞት ተለይቶ የሚሄድበት ጊዜው እንደደረሰ ነርሯቸዋል፡፡ ነገሩም እውነት መሆኑን ለማስረዳት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮኛል የሚል ቃል ጨምሮ ጽፎላቸዋል፡፡

**የመልእክቱ አከፋፈል፡-**

2ኛይቱ የጴጥሮስ መልእክት ሦስት ምዕራፎች አሉት፡፡ እነዚህንም ምዕራፋት በአምስት ክፍለን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

1. መግቢያ (1÷1-3)
   - ላኪው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ መሆኑንና የተቀባዮቹንም ማንነት በጥቂቱ (1÷1)
   - ለተቀባዮቹ ያቀረበው የቅዱስ ጴጥሮስ ሰላምታ (1÷2-3)
2. የተሰበከላቸው ትምህርት እውነተኛ እንደሆነ (1÷4-21)
   - ከፊት ይልቅ ትጋትን እንዲያስቡ የጻፈላቸው ማነቃቂያ ትምህርት (1÷4-15)
   - የጌታን ግርማ አይቶ የአብን ድምፅ ሰምቶ የጸና የትንቢት ቃል ይዞ እንዳስተማራቸው (1÷16-21)
3. በመካከላቸው ስለነበሩት የሐሰት አስተማሪዎች ማንነት (2÷1)
   - መናፍቃን፣ ደፋሮች፣ ተሳዳቢዮች፣ አመፀኞች፣ ዕውቀት የጎደላቸው፣ ስለ መሆናቸው፣ የባለአምን መንገድ ስለ መከተላቸው፣ የፈጠራቸውን አምላክ ስከመሳደብ ድረስ ደፋሮች ስለመሆናቸው፣ በእነርሱ ክፍ ሥራ ምክንያት የእውነት መንገድ እንደምትሰደብ እና ለዚህ ሁሉ ጥፈታቸው ዋጋቸውን የሚቀበሉበት ቀን ቅርብ ስለመሆኑ በስፋት ጽፎላቸዋል (2÷1-16)፡፡
   - መናፍቃን በዓለም የተሸነፉ አንድምውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ ትተው ወደመጡበት ኃጢአትና ርኩሰት የተመለሱ ስለመሆናቸው፣ ራሳቸው በኃጢአት ባርነት ተይዘ እያሉ

አርነት ትወጣላችሁ እያሉ በከንቱ ተስፋ ሌሎችን እንደሚያታልሉም ጭምር በዝርዝር ጽፎላቸዋል(2÷17-22)

4. ስለ ዳግም ምጽአት የጻፈው ትምህርት (3÷1-16)
   - ነቢያት የተነበዩትን በሐዋርያትም የተሰበከውን የጌታን ትእዛዝ እንዲያስቡ አንድም እንዳይነገና ቸልተኞች እንዳይሆኑ ጽፎላቸዋል (3÷1-2)
   - የጌታን ዳግመኛ መምጣት የሚክዱ ዘባቾች መኖራቸውን ጠቅሶ ለዘባቾቹ የሐሳት ትምህርት መልስ ሰጥቶበታል (3÷3-10)
   - ምእመናን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽአት ቀንን ያለ ነቀፋ ሆነው እንዲጠብቁ (3÷11-14)
   - ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጻፈላቸው መልእክቱ ስለ ዳግም ምጽአትናክርስቲያኖች ቀኑን እንዴት ባለ ሁኔታ መጠበቅ እንደሚገባቸው የታፈላቸውን እንዲያስታውሱ ያሳስባቸዋል (3÷15-16)
5. ማጠቃለያ (3÷17-18)
   - የአመፀኞችንትምህርት ሰምተው እንዳይሳሳቱ ይልቁንም በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት ማደግ እንደሚገባቸው የሰጣቸው ማሳሰቢያ (3÷17) እና ለጌታ ለጌታ ያቀበረው ምስጋና (3÷18)

**መልእክተ ዮሐንስ ሐዋርያ**

**መግቢያ**

ዮሐንስ የስሙ ትርጉም ፍስሐ ወሀሴት ማለት ነው፡፡ "ወብዙኃን ይትፌስሑ በለደቱ እንዲል፡፡ (ማቴ 10÷3 እና ሉቃ.1÷13)፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ብዙ የግብር ስሙችም አሉት፡፡ እነሱም

1. ፍቁረ እግዚእ ይባለል፡- ጌታ ይወደው የነበረ ደቀመዝሙር ሲራ ራሱን ገልጾታል (13÷23፣ 19÷29፣ 20÷2፣ 21÷20)፡፡ ጌታ የሚወደው ማለቱም ጌታ ሌሎችን ሐዋርያት የማይወድ ሁኖ አይደለም፡፡ በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከመጨረሻው እንደወደዳቸው በወንጌሉ ተመዝግበል (ዮሐ.13÷1፣ 15÷12)፡፡ መምህር ከተማሪዎቹ መካከል በጠባዩ መልካም፣ በትምህርቱ ጉበዝ የሆነውን ለይቶ እንደሚወደው ሁሉ ጌታም እሱ ባወቀው ከሌሎች አብልጦ ያቀርበው እንደነበር ለመናገር ነው እንጂ፡፡

2.ታዎሎጉስ/ታዖጉሎስ ይባላል፡- ይህም ነበቤመለኮት ማለት ነው፡፡ የምሥጢረ ሥላሴን ነገር አምልቶ አጉልቶ ስለጻፈ የወጣለት ስም መሆኑን ሊታውንት ይስማሙበታል (1÷1)፡፡

3. ወልደ ነጐድጓድ ተብሏል፡- ደቂቀ ምሥጢር ማለት ነው፡፡

**የዮሐንስ ትውልድ**

- ዮሐንስ አባቱ ዘብዴዎስ እናቱ ማርያም ባውፍልያ ይባላሉ
- ከዓሳ አጥማጅነት ተጠርቷል። ማቴ. 4፡21
- ከ4ቱ ኪሩቤል በገጸንስር ይመሰላል
- ከ4ቱ አፍላጋት በፈለገ ኤፍራጥስ ይመሰላል
- ከ4ቱ ክፍለ ዘመን በወርኃህጋይ/በበጋ/ ይመሰላል
- ከ4ቱ አንስተያዕቆብ በራኄል ይመሰላል
- የጌታን ስዕል ለመጀመሪያ ጊዜ ከለሜዳ አስታጥቆ የሳለ ወንጌላዊ ዮሐንስ ነው።
- ቅዱስ ዮሐንስ ከሌሎች ሐዋርያት ልዩ የሚአደርገው መከራውን ሳይሳቀቅ ቀራንዮ አደባባይ ድረስ የተከተለው እሱ ብቻ በመሆኑ እመቤታችንን በእናትነት በአደራ ተቀብሏል። ዮሐ. 19፡26

**ያስተማረበት ሀገር**

ለተገረዙት ሐዋርያ በመሆን ከጴጥሮስ ጋር የስብከት ስራውን በኢየሩሳሌምና በአካባቢው የጀመረው ዮሐንስ ወደ አንበጾኪያ ሂዶ ያስተማረውም ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ነበር። እንደ ስንክሳሩ አገላለጥ ከኢየሩሳሌም እስከ አንጾኪያ በፈረስ 20 ቀን ያስኬዳል። ነገር ግን በእግዚአብሔር አጋዥነት በአንድ ቀን እንደደረሰ ይናገራል። ወደዚህች ሀገር ሲገባም  የሀገሩ ሰዎች እጅግ ክፉዎች እንደሆኑ ተመልክቶ አዝኖ ሳለ ቅዱስ ጴጥሮስ አብረታትቶት አብረው ወደ ከተማ ገብተው በክርስቶስ ስም ወንጌል ሰብከዋል። ምንም እንኳ ከመምላክያነ ጣዖት ብዙ መከራ ቢደርስባቸውም በአንጾኪያ ውስጥ ታምራትን እያደረጉ ብዙ ሕሕዛብን አሳምነዋል።

ቅዱስ ዮሐንሰ ከአንጾኪያ ሌላ በሎዶቅያም እንዳስተማረ መጽሐፈ ስንክሳር ይገልጣል። በዚያ እያስተማረ በነበረበት ጊዜ በከተማ አጠገብ ያለ ቂድሮስ የሚባል ወንዝ ሞልቶ የሀገሪቱን ንብረት ባወደመ ጊዜ በታምራት ውኃውን አቆመላቸው ወደከተማዋም ገብቶ ብዙ ታምራትን እያደረገ ወንጌልን ሰበከ። ብዙ ሰዎችም ካዩት ታምራትና ከሰሙት ትምህርት የተነሣ በወንጌል አምነው ተጠመቁ። /ስንክሳር ሐምሌ 5/

ዮሐንስ በህይወቱ መጨረሻ አካባቢ ያስተማረው በእስያ ሀገር በአፌሶን ከተማ ነው። በዚህች ከተማ ውስጥ ከእርሱ አስቀድሞ ቅዱስ ጳውሎስ በኋላም የመንፈስ ልጁ ጢሞቴዎስ እንዳስተማሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን። (የሐዋ.19÷1-41፣ 1ኛ.ሞቴ.1÷9)። የቤተክርስቲያን ትውፊታዊ ታሪክ እንደሚአስረዳው ዮሐንስ ወደዚህ ከተማ የመጣው ከደቀመዝሙሩ ከአብሮ ኵሮስ ጋር ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በኤፌሶን በሚአስተምርበት ጊዜ ከኔሮን ቄሣር ቀጥሎ በሮም የነገሠው ድምጥያኖስ የራሱን ምስል አሠርቶ እንዲሰገድለት ወደአፌሶን ልኮ እንደነበርና ዮሐንስ ከምእመናን ጋር ሁኖ ይህን ድርጊት እንደተቃወመ በቤተክርስቲያናችን ታሪክ ተመዝግቧል።

ዮሐንስ ይህን ተቃውሞ በማቅረቡ ወደ ሮም ተወስዶ ከተፈረደበት በኋላ በመንግሥት ላይ ያመጹ ሁሉ በሚታሰሩበት በደሴተፍጥሞ እንዲታሰር ተደረገ፡፡

### ዕረፍቱ

ስለሐዋርያው ዮሐንስ የመጨረሻ ሕይወት ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች አሉ፡፡

1. በዮሐንስ ወንጌል (21÷20-23) ላይ ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን ስለ ዮሐንስ በጠየቀው ጊዜ ጌታ ደግሞ "እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ; (ማቴ.16÷28) ብሎ የመለሰለትን ቃል መሠረት አድርገው ዮሐንስ ሞትን አልቀመሰም የሚሉ አሉ፡፡
2. ሌሎች ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል (20÷22-23) እና በማርቆስ ወንጌል (10÷38-39) የተጻፈውን ቃል በመጥቀስ ዮሐንስ እንደሌሎቹ ሐዋርያት ሙቷል ይላሉ፡፡

የጉባኤ ቤት ምምህራንና አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን አስትህሮም ወንጌላዊ ዮሐንስ አልሞተም ይልቁንም ተሰውሯል በሚለው ይስማሙበታል፡፡ በዚህም መሠረት የተሰወረበት የመታሰቢያ በዓል ጥር 4 ቀን ይከበራል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ከወንጌሉ በተጨማሪ 3 መልእክታትን ጽፏል፡፡

### የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስ  ሦስቱ መልእክታት

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የዮሐንስ መልእክታት የሚባሉ ሦስት ናቸው፡፡ ነገር ግን በሦስቱም መልእክታት መጀመሪያ ላይም ሆነ በውስጣቸው የዮሐንስ ስም አይገኝም፤ ይሁን እንጂ አራተኛውን ወንጌል የጻፈው ዮሐንስ ሐዋርያው እንደሆነ ከጥንት ጀምሮ የታመነ ነው፡፡ የዮሐንስ ደቀ መዝሙር እንደሆነ የሚነገርለት ፓሊካርፕ የተባለው የቤተክርስቲያን አባት ወደ ፊልጵስዩስ በጻፈው ጽሑፍ ውስጥ እነዚህ ሦስቱን መልእክታት ዮሐንስ እንደጻፋቸው መስክሯል፡፡
ከዚህም ሌላ ፓፒያስ፣ አውሳብዮስ፣ ኤሬንየስ፣ የእስክንድርያው ቀሌምንጦስ እነዚህ መልእከታት የሐዋርየው የዮሐንስ ጽሑፎች መሆናቸውን በየጽሑፋቸው ገልጸው ተናግረዋል፡፡ የመልክታተ ይዘትና በውስጣቸው የሚገኙት ኃይለ ቃላት፣ ቋንቋቸውም ከዮሐንስ ወንጌል ጋር ስለሚመሳሰሉ ጸሐፊያቸው ወንጌላዊ ዮሐንስ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ዮሐንስ እነዚህን መልእክታት የጻፈበት ቦታ ኤፌሶን ሲሆን፣ የጻፈበትም ዘመን በ90 ዓ.ም ገደማ መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ፡፡

### መጀመሪያይቱ የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት

ሁለተኛ የሚጽፍ ነውና ቀዳማዊ አለ፡፡ ይህች መልእክተ ለማን እንደተጻፈች የሚገልጽ ቃል በውስጧ አልተመዘገበም፡፡ ነገር ግን ዮሐንስ ያስተማራቸው ክርስቲያኖች ስለመሆናቸው "ልጆቼ ሆይ" እያለ በጻፈው ቃል መረዳት ይቻላል(2÷1፣ 3÷18)፡፡ዮሐንስ በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ለረጅም ጊዜ ወንጌልን የሰበከው በኤፌሶን መሆኑ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ታውቆአል፡፡ በኤፌሶን

ከተማ ብቻ ሳይሆን በመላዋ እስያ የክርስቶስን ወንጌል አስፋፍቶአል። ስለዚህ ዮሐንስ ይህቺን መልእክት የጻፈላቸው ሰዎች በእስያ አብያተ ክርስቲያናት የነበሩ ክርስቲያኖች እንደሆኑ ብዙዎች መምህራን ያምናሉ። በሌላ በኩል ደግሞ መልእክቲቱ ከአጠቃላይ መልእክታት አንዷ እንደ መሆኗ መጠን ዮሐንስ የጻፋት በአንድ ቦታ ላሉ ለተለዩ አብያተ ክርስቲያናት ሳይሆን፤ በየትኛውም ስፍራ የሚገኙ ክርስቲያኖች እንዲያነቡለት ነው፣ የሚለው በብዙዎች ሊቃውንት ተቀባይነት ያለው አመለካከት ነው።

### የተጻፈበት ምክንያት፡-

ምክንያተ ጽፈቱን ቅዱስ ዮሐንስ መሲሕ እያለ ሲያስተምር ሰምቶ ድምጥያኖስ አስሮ አግዞታል፤ ከታሰረ ከሰባት ዓመታት በኋላ ድምጥያኖስ ሙቶ ልጅ ጠራብያኖስ ሲነግሥ ዮሐንስን ከእስራቱ ፈታው። ነገር ግን ደቀመዝሙር ከመምህሩ ከተለየ ክህደት፣ ኑፋቄ ማንቃት ልማድ ነውና ደቀመዛሙርቱ 1ኛ ሙቶ አልተነሣም 2ኛ ሙቶ የተነሣው ቀደማዊ አይደለም 3ኛ በብርሃን የሚሠራውን እንጅ በጨለማ የሚሰራውን አያውቅም በነቢብ በገቢር የሚሰራውን እንጅ በሐልዮ የሚሰራውን አያውቅም ብለውታል። 4ኛ አንድ ጊዜ ካመኑ ከተጠመቁ ምን ምግባር ያሻል ብለውት ነበርና የመጀመሪያውን መልክት የጻፈበት ምክንያት ለእዚህና መሰል ኑፋቄዎች መልስ ለመስጠት እንደሆነ ይታመናል።

### የተጻፈበት መሠረታዊ ዓለማ፡-

የመጀመሪያይቱ የዮሐንስ መልእክት የተጻፈችበት ምክንያት በዚያ ዘመን ከተነሡት የሐሰት መምህራን እንዲጠበቁ ምእመናንን ለማሳሰብ ነው። (2÷26) እነዚህን ሰዎች ዮሐንስ "የክርስቶስ ተቃዋሚዎች" (Antichrists) በማለት ይጠራቸዋል (2÷18)።

### የመልእክቱ አጠቃላይ ይዘት

አንደኛይቱ የዮሐንስ መልእክት የያዘችው የሃይማኖትና የምግባር ትምህርት ነው። ዮሐንስ "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" በማለት ይናገራል። (4÷9-16)። ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ይገልጣል አስቀድሞ የወደደን እርሱ ነው። (4÷19)። ይህንንም ፍቅሩን የሰጠው ልጁን የኃጢአታችን ማስተስረያ አድርጐ በመላክ ነው (4÷9-10) ልጁም ነፍሱን ስለ እኛ አሳልፎ ሰጠ፣ በዚህም ፍቅርን አውቀናል (3÷16)። ስለዚህ እኛም እርስ በእርስ ስንዋደድ ነፍሳችንን ለወንድሞቻችን እስከመስጠት ድረስ መሆን አለበት (3÷16)። በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት መዋደድ የለብንም (3÷17-18)። የእርስ በእርስ መዋደድ ባለበት እግዝአብሔር ይገኛል (4÷12) ፍቅሩም ፍጹም ይሆናል። ይህም ለእኛ በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆናል (4÷17) ፍጹም

ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል፣ የሚፈራ ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም (4÷17-18) በማለት ስለ ፍቅር ሰፊ ትምህርት ይሰጣል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በፍቅር አንጻር ስለ ጥላቻም አንሥቷል፡፡ ወንድሙን የሚጠላውን ሰው በቃየል መስሎ "ነፍሰ ገዳይ" ብሎ ይጠራዋል (3÷12-15)፤ ወንድሙን የሚጣላ ሰው በብርሃን አለሁ እያለ በጨለማ እደሚኖርም አብርራርቷል (2÷9)፡፡

**የመልእክቱ አከፋፈል**

የመጀመሪያይቱ የዮሐንስ መልእክት አምስት ምዕራፎች አሏት፡፡ እነርሱንም በአምስት ክፍሎች እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

1. መግቢያ (1÷1-4)
   - ላኪው ያየውን የሰማውንና የዳሰሰውን እንደሚመሰክር (1÷1)
2. ከኃጢአትና ከዓለም ምኞች ተለይተው በብርሃን እንዲኖሩ የጻፈው ትምህርት (1÷5)
   - በጨለማ የሚመላለስ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንደሌለው (1÷5-7)
   - ኃጢአትን አምኖ ቢናዘዙ ይቅርታ እንደሚገኝ (1÷8-10)
   - የጌታን ትእዛዛት መጠበቅ እንጂ፤ ኃጢአትን ማድረግ እንደማይገባ (2÷1-6)
   - ትእዛዛቱን የሚጠብቅ በብርሃን የማይጠብቅ ደግሞ በጨለማ እንደሚኖር (2÷7-11)
   - ዓለምንና በዓለም ያለውን እንዳይወዱ በየዕድሜአቸው የጻፈላቸው ምክር (2÷12-17)
3. የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ከሆኑት ሐሰተኞች እንዲጠበቁ የጻፈው ትምህርት
   - የሐሰተኞቹን ማንነት አውቀው በተማሩት ጸንተው እንዲኖሩ (2÷18-29)
   - በክርስቶስ የሚኖሩ የእግዚአብሐር ልጆች ኃጢአት እንደማያደርጉ (3÷1-10)
   - ፍቅርን እንዴት እንዳወቅነው (3÷11-24)
   - የእውነትና የስህተት መንፈስ በምን እንደሚለይ (4÷1-6)
4. ስለ ፍቅር የጻፈው ትምህርት (4÷7-21)
   - እግዚአብሔር እኛን በወደደበት ፍቅር እርስ በእርስ እንድንዋደድ (4÷7-12)
   - ፍጹም ፍቅር እንዲኖረን (4÷13-21)
5. በእግዚአብሔር ልጅ ስለማመን የጻፈው ትምህርት (5÷1-7)
   - ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ነው ብሎ ማመንና መታመን እንዲገባ (5÷1-5)
   - እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ስለመሆኑ የጻፈው ቃል (5÷6-21)

## ሁለተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት

### የተጻፈችላት ሴት

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ሁለተኛይቱን መልእክት የጻፈው ለአንዲት ለተመረጠች እመቤትና ለልጆችዋ ነው (ቁ.2)። የእኛ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳው ይህቺ ሴት በአንዲት ደሴት የምትኖር የነገሥታትን፣ የመኳንንቱን ልጆች የምታሳድግ እመቤት ነበረች። ዮሐንስ ከደቀ መዝሙሩ ከአብሮኮሮስ ጋር በቤርያ ገብቶ በክርስቶስ አሳምኖአት ከዚያ ወጥቶ ከሄደ በኂላ ይህን መልእክት ጽፎላታል። በእኛ ቤተክርስቲያን ባለው የዚህች መልእክት ትርጓሜ መግቢያ ላይ የተመረጠችው እመቤት ስሟ "ሮምና" እንደምትባል ተገልጦአል። መልእክቲቱ የተላከችው ክርስቲያን ለሆነች ለአዲት የተመረጠች እመቤትና ለልጆችዋ መሆኑን ያስረዳል። ዮሐንስ በዚህች መልእክት ውስጥ ራሱን "እኔ ሽማግሌው (ቀሲስ)" ብሎ ይጠራል (ቁ.1)። የተመረጠች እመቤትና ልጆችዋን ይወዳቸዋል (ቁ.1)፤ በእውነት ስለሚሔዱ ደስ ብሎታል (ቁ.4)፤ ብዙ ሊጽፍላቸው ፈልጐ ነበር። ነገር ግን ሊሔድና አፍ ለአፍ ሊያነጋግራቸው ተስፋ ስላደረገ ባጭሩ ሊጽፍ ችሎአል። (ቁ.12)።

### የተጻፈበት ዋና ዓላማ

ቅዱስ ዮሐንስ ይህቺን መልእክት የጻፈበት ዋና ዓላማ በአንደኛው መልእክት ከተገለጠው ጋር አንድ ዓይነት ነው። በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማያምኑ ብዙ አሳቾች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ስለነበሩ እነዚህን ሰዎች እንዳይቀበሉ ለማሳሰብ ጽፎአል (ቁ.7÷10)

### የመልእክቱ አጠቃላይ ይዘት

ሁለተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት በቅድሚያ የሥነ ምግባር ቀጥሎም የሃይማኖት ትምህርት ታስተምራለች።

### የመልእክቱ አከፋፈል

ሁለተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት አጭር ስለሆነች በምዕራፋት አልተከፈለችም፣ ስለዚህ ያሉአትን 13 ቁጥሮች በመጠቀም በአራት ክፍለን እንመለከታለን።

1. መግቢያ (ከቁ.1-3)
   - የጸሐፊው ፍቅር (ቁ.1፡2)
   - ለተቀባዮቹ ጸሐፊው ያቀረበው ሰላምታ (ቁ.3)
2. እርስ በእርሳቸው እንዲዋደዱ የጻፈላቸው ቃል (ከቁ.4-6)

- በእውነት በሚሔዱት ልጆች የተሰጠው ደስታ (ቁ.4)
- እርስ በእርስ በመዋደድ ትእዛዝ እንዲሔዱ (ቁ.5-6)

3. ከክርስቶስ ተቃዋሚዎች እንዲጠበቁ የጻፈላቸው ትምህርት (ከቁ.7-11)

- እንዳይቀበሉአቸው የጻፈው ማሳሰቢያ (ከቁ.7-11)

4. ማጠቃለያ (ቁ.12፡13)

- ወደ ተቀባዮች ለመሔድ ያለው ታሪክ (ቁ.12)
- ለተመረጠችው እመቤት ከእኅቷ ልጆች የቀረበላት ሰላምታ (ቁ.13)

**ሦስተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት፡-**

ሦስተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት የተጻፈችለት ሰው ጋይዮስ ይባላል፡፡ ይህ ጋይዮስ ከደርቤኑ ጋይዮስና ከቆሮንቶስ ጋይዮስ የተለየ ነው፡፡ ጸሐፊው በእውነት እንደሚወደው ገልጦአል፡፡ (ቁ.1) ወንድሞችም ወደ ዮሐንስ መጥተው ጋይዮስ በእውነት በክርስትና ሕይወት የሚሔድ ሰው እንደሆነ መስክረውለታል፡፡ (ቁ.3)

የዮሐንስ ጋይዮስን "ልጆቼ" ብሎ ከሚጠራቸው መካከል አድርጐ ቆጥሮታል፡፡ (ቁ.4) ክርስትናንም የተቀበለው በእንግዳ ተቀባይነት ነው፣ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ለሚገኘው የሦስተኛይቱ ዮሐንስ ትርጉም ላይ ጋይዮስ በቀላውዴዎስ ቄሳር የተሰደዱትን እንግድነት ይቀበል እንደነበር፣ እያበላ እያጠጣ፣ እያሳደረ፣ ስንቅ እየሰጠ እየሸኘ ይሰዳቸው እንደነበር ተገልጦአል፡፡ በመልእክቲቱ ውስጥም ከአሕዛብ ምንም እርዳታ ሳያገኙ የወጡትን ወንድሞች (ክርስቲያኖች) እንግድነት ይቀበል እንደነበር በገዞአቸውም ይረዳ እንደነበር ተመስክሮለታል፡፡ (ቁ.5-8)፡፡

በሁለተኛው መልእክት እንደ አደረገው ራሱን "ሽማግሌው" ብሎ ጠርቷል፡፡ (ቁ.1) ሊጽፍለት የፈለገው ብዙ ነገር ቢኖረውም በአካል ሄዶ ሊሠጠውና አፍ ለአፍ ሊያነጋግረው ተስፋ ስላደረገ ባጭሩ ሊጽፍለት ችሎአል፡፡ (ቁ.13-14)

**የተጻፈበት ዋና ዋና ዓለማዎች፡-**

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ሦስተኛይቱን መልእክት ለጋይዮስ የጻፈፈበት መሠረታዊ ዓላማ ሁለት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

1. በእውነት እየሔደ እንግዶችን በመቀበል ስላደረገው መልካም ሥራ ሊያመሰግነውና በዚህ በጐ ሥራ እንዲቀጥል ሊያበረታታው ነው (ቁ.8)
2. በጐ የሆነው እንጂ ክፉ የሆነውን እንዳይመስል ሊያሳስበው ጽፎለታል (ቁ.10)

**የመልእክቱ አጠቃላይ ይዘት**

ሦስተኛውየዮሐንስ መልእክት ይዘቱ የሥነ ምግባር ትምህርት ነው። ዮሐንስ ለጋይዮስ በነገሩ ሁሉ እንዲከናወንለትና ጤና እንዲኖረው ይጸልይለት ነበር (ቁ.1)። ክርስቲያን ስለ ሌላው ኑሮና ጤንነት መጸለይ እንደሚገባው ከዚህ እንማራለን። ክርስቲያን እንደ ጋይዮስ በእውነት የሚሔድ መሆን አለበት፤ ይህም እጅግ የሚያስደስት ነው (ቁ.2-4)። እንግዶችን መቀበል ደግሞ ከፍቅር የተነሣ የሚሠሩት ምግባር ነው (ቁ.5፡6) ። በተለይም ስለ ክርስቶስ ስም አሕዛብ የሚያሳድዱአቸውን ወገኖች በእንግድነት መቀበል ተገቢ መሆኑን መልእክቲቱ ታስተምራለች (ቁ.7-8)። ጋይዮስ በጐውን እንጂ ክፉውን እንዳይመስል ይጽፍለታል (ቁ.11)። ክርስቲያን የዲዮጥራጢስን የትዕቢትና የክፋት መንገድ ትቶ የዲሜጥሮስን ሕይወት ሊከተል ይገባዋል። ምክንያቱም በጐ የሚያደርግ ከእግዚአብሔር ነው፤ ክፉ የሚያደርግ ግን ከእግዚአብሔር አይደሉምና ነው (ቁ.11)።

### የመልእክቱ አከፋፈል

ሦስተኛይቱ የዮሐንስ መልእክት እንደ ሁለተኛይቱ መልእክት በምዕራፋት አልተከፈለችም። ነገር ግን ያሉአትን 15 ቁጥሮች በአራት ክፍለን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

- መግቢያ (ከቁ.1-3 )
- ላኪውና ተቀባዩ (ቁ.1)
- ዮሐንስ ስለ ጋይዮስ ያቀረበው ጸሎት (ቁ.2)
- ስለ ጋይዮስ እውነተኛነት የወንድሞች ምስክርነት (ቁ.3፡4)

1. የጋይዮስ እንግዳ ተቀባይነት (ከቁ.5-8)
   - ስለ ጌታም ከአሕዛብ የወጡ ወንድሞችን በእንግድነት ተቀብሎ ያሳየው የፍቅር ሥራ (ከቁ.5-7)
   - እንዲህ ያሉትን በእንግድነት መቀበል ለክርስቲያኖች እንደሚገባ (ቁ.8)
2. የዲዮጥራጢስ መወቀስና የዲሜጥሮስ መመስገን (ከቁ.9-12)
   - ስለ ዲዮጥራጢስ ክፋት የጻፈው ወቀሳ (ቁ.9፡10)
   - በጐውን እንጂ ክፉውን እንዳይመስል ለጋይዮስ የተላለፈ ምክር (ቁ.11)
   - ስለዲሜጥሮስ በጐነት የጻፈው ምስክርነት (ቁ.12)

3. ማጠቃለያ (ከቁ.13-15)
   - ሔዶ እንዳየውና ስለሰጠው ተስፋ (ቁ.13፡14)
   - የስንብት ሰላምታ (ቁ.15)

### የያዕቆብ መልእክት

የዚህች መልእክት ጸሐፊ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እንደሆነ በርእሱ ላይ ተገልጦአል፡፡ያዕቆብ ማለት አዕቃዲ፣ አኃዚ ማለት የቀደመ ያዕቆብ /የይስሐቅ ልጅ/ አዕቃጼ ሰኰና ኤሳው እንደነበር ይህኛው ደግሞ አዕቃጼትምህርተ መናፍቃን ነውና ያ ሰኰናኤሳውን ይዞ እንደተወለደ እሱም ሰኰና ወንጌልን ይዞ እያስተማረ ኑሯልና፡፡

ከ12ቱ ሐዋርያት መካከል፣ "ያዕቆብ" በሚለው ስም የተጠሩ ሁለት ሐዋርያት አሉ፡፡ አንዱ የዘብዴዎስ ልጅ የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ (ታላቁ ያዕቆብ) ሲሆን ሌላው ደግሞ የእልፍዮስ ልጅ የተባለው ታናሹ ያዕቆብ ነው፡፡ ይህም የታወቀው ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ "… ነገር ግን ከጌታ ወንድም ከያዕቆብ በቀር ከሐዋርያት ሌላ አላየሁም ብሎ በጻፈው ቃል ነው፡፡" (ገላ.1÷9) ይህም ቃል የያዕቆብን ሐዋርያነት ያሳያል፡፡

ያዕቆብ "የጌታ ወንድም" ተብሎ በብዙ ቦታ ተጠርቶአል (ማቴ.13÷55፤ ገላ.1÷19)፡፡ የጌታ ወንድም /እኁሁ ለእግዚእነ/ ያለበት ምክንያት፡-

1ኛ.በተዛምዶተ ሥጋ ነው ይህም ማለት ያዕቆብ የዮሴፍ ልጅ ነው፡፡ መገናኛው ጉንዱ /ቅድመ አያታቸው/ አልዓዛር ይባላል፡፡ አልዓዛር ማትያንና ቅስራን ይወልዳል፡፡ ቅስራ ደግሞ ኢያቄምን ኢያቄም እመቤታችንን እመቤታችን ጌታን ትወልዳለች፡፡ ማትያን ያዕቆብን፣ የዕቆብ ዮሴፍን፣ ዮሴፍ፣ ያዕቆብን ይወልዳል፡፡ ዮሴፍና የጌታ እናት ድንግል ማርያም ደግሞ በቅድመ አያታቸው በአልዓዛር በኩል ይዛመዳሉና ስለዚህ ያዕቆብ የጌታ ወንድም ሊባል ቻለ የሚል ነው፡፡

2ኛ.አብሮ በማደግ ነው፡፡ የያዕቆብ እናቱ በሕፃንነቱ ሙታበት እመቤታችን ከጌታ ጋር ጡት እያጠባች አሳድጋዋለችና፡፡ ይህስ አይሆንም ሐሊብ ድንግልናዊትን ካንድ ከጌታ በቀር የጠባ የለም ብሎ የጌታ ወንድም የተባለ ከጌታ ጋር ካባቱ ከዮሴፍ ቤት አብረው በማደጋቸው ነው፡፡
ያዕቆብ ስምኦን እና ይሁዳ የተባሉ ወንድሞች እና ስማቸው ያልተገለጠ እኅቶችም እንደነበሩት ከወንጌል እንረዳለን (ማቴ 13÷55)፡፡ እነዚህ ሁሉ የደራሲው የዮሴፍ ልጆች ናቸው ያዕቆብ የሁሉም ታናሽ መሆኑን ስንክሳር ይናገራል፡፡[1]

ያዕቆብና ወንድሞቹ ጌታ በሚያስተምርበት ጊዜ እየሔዱ ይጉበኙት ነበር (ማቴ.12÷46-50፣ ዮሐ.7÷5)፡፡ ነገር ግን ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ለያዕቆብ እንደታየው ተገልጦአል፡፡ (1ኛ ቆሮ.15÷13-21)፡፡ በዚህም በክርስቶስ ማመኑ የተረዳ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ግን ትንሣኤውን አይቶ አመነ ይላሉ፡፡ ከጌታ ዕርገት በኋላ ሐዋርያት በሰገነት ቤት ውስጥ ለጸሎት በሚተጉበት ጊዜ ያዕቆብ አብሮ ነበር፤ ስለዚህ መንፈስ ቅዱስን ከሐዋርያነት ጋር አብሮ ተቀብሎአል ማለት ነው፡፡

[1]ስንክሳር ሐምሌ 18

(የሐዋ.ሥራ 1÷13)። ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ጴጥሮስን እስከ አሰረውና መልአኩ እስከፈታው ጊዜ ድረስ ከጴጥሮስ ጋር የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ እንደነበር በሐዋርያት ሥራ (12÷7) ተገልጾ እናገኛለን።

በ50 ዓ.ም በተካሄደው የኢየሩሳሌም ጉባኤ ላይ የጉባኤው መሪ ነበር (የሐዋ.ሥራ 15÷13-21)። ቅዱስ ጳውሎስ 3ኛውን ሐዋርያዊ ጉዞውን በ58 ዓ.ም ሊያጠናቅቅ ወደ ኢየሩሳሌም በሔደ ጊዜ ወደ ያዕቆብ ዘንድ እንደገባ ተገልጦአል (የሐዋ.ሥ 21÷18)። እነዚህ ሁሉ መረጃዎች ያዕቆብ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ እንደነበር ያሳያሉ።

## የቅዱስ ያዕቆብ ዕረፍት

ስለ ያዕቆብ የቅድስና ሕይወት በዝርዝር የጻፈው ሄጊስጳስ (Hegesppus) የተባለው ሰው ያዕቆብ በሰማዕትነት የሞተው በአይሁድ ሸንጐ (Sanhedrin) እንደሆነና የሞተበትም ጊዜ 62 ዓ.ም ገደማ እንደሆነ ገልጿል። የእስክንድርያው ቀሌምንጦስ ይህንኑ በመጽሐፈ ስንክሳርና ገድለ ሐዋርያት ላይ ስለ ዕረፍቱ የመዘገበው ታሪክ እንዲሁ ተመሳሳይ ነው። ያዕቆብ በኢየሩሳሌም ውስጥ የተለያዩ ተአምራትን እያደረገ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብዙ ጊዜ ካስተማረ በኋላ አይሁድ በሚያደርገው ተአምራትና በሚሰብከው ስብከት ብዙዎች በክርስቶስ ማሳመኑን ሲያውቁ ያዙት። ያዕቆብም በሸንጐው ፊት ቀርቦ ለተጠየቀው ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ ሰጠ፤ ስለኢየሱስ ክርስቶስም መለኮታዊነት፣ ከአብ ጋር ዕሩይ መሆኑን በመድረክ ላይ ሆኖ መሰከረ፤ በዚህን ጊዜ ከመድረክ አውርደው ደበደቡት፤ በኋላ ከመካከላቸው አንድ ሰው ጫፉ ብረት በለበሰ ዱላ ራስ ራሱን ብሎ መታውና ገደለው።[2]በዓለ እረፍቱም ሐምሌ 18 ቀን ይከበራል።

## የጻፈላቸው ሰዎች

የያዕቆብ መልእክት ለማን እንደተጻፈ በመግቢያዋ ላይ ስትናገር ለተበተኑት ለ12ቱ ወገኖች ትላለች (1÷1)፤ እነዚህም ሕዝበ ዲያስጶራ (Diaspora) የሚባሉት ናቸው። “ሕዝበ ዲያስጶራ” ማለትም በዝርወት ያሉ ሕዝብ ማለት ነው። አይሁድ በየምክንያቱ ተሰደው በየአሕዛብ አገሮች ሁሉ ተበትነው እንደሚገኙ ይታወቃል። እነዚህም ሰዎች ወንጌል ተሰብኮላቸው ክርስቲያን ሆነዋል (2÷1)፤ (5÷14)። በልዩ ልዩ ፈተና ውስጥም ይገኙ ነበር (1÷2፡3)። ያዕቆብ ለእነዚህ ሰዎች ይህቺን መልእክት የጻፋት ይሁን እንጂ መልእክቲቱ በዓለም ሁሉ ላሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የተጻፈች አጠቃላይ መልእክት መሆኗ የታወቀና የተረዳ ነው።

---

[2]ገድለ ሐዋርያት

## የተጻፈችበት ቦታ እና ዘመን

ያዕቆብ ከገድሉ ጽናት የተነሣ ወኮነ እግሩ ከመእግረገመል ይለዋል፡፡ እግሩ እንደግመል እግር ሁኖ ነበር፡፡ ሐዋርያት ለሰብከተወንጌል አይፋጠንም ብለው በኢየሩሳሌም ኤጲስቆጶስነት ሹመውት ሂደዋል፡፡ ይህሰ እንዳይሆን ሐዋርያ ደመና ጠቅሶ ካሰበው ደርሶ ብዙ ሰው አስተምሮ አሳምኖ መዋል ይችላል ከሐዋርያትም አንድ አንድ ደዌ የሌለበት የለም ቅዱስ ጴጥሮስን ድው የሥጋ ይለዋል ቅዱስ ጳውሎስንም ተውህበኒ መልአከሰይጣን ዘይደጉጸኒ ሥጋየ ወይኰርአኒ ርእሰየ ይለዋል ብሎ በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁድ ምሁራነ ኦሪት ነበሩ እሱም ምሁረ ኦሪት ነበርና ከሱ በቀር ተከራክሮ የሚረታቸው ሌላ የለም ብለው ሹመውታል፡፡ ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ እንዲሉ አንድም እጣው እንደሆነች አውቀው ሹመውታል፡፡ በሰማዕትነት እስከሞተበት ጊዜ ድረስ የነበረው በኢየሩሳሌም ስለነበር መልእክቲቱንም የጻፋት በኢየሩሳሌም በ50 ዓ.ም ገደማ እንደሆነ መምህራን ይናገራሉ፡፡

## የተጻፈበት ዋና ዋና ዓለማዎች፡-

የያዕቆብ መልእክት የተጻፈችባቸው ዋና ዋና ዓለማዎች ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

1. በየአገሩ የተበተኑት የአይሁድ ክርስቲያኖች ልዩ ልዩ ፈተና ደረሰባቸው ስለነበር ፈተናውን (መከራውን) ደስ እያላቸው በትዕግሥት እንዲቀበሉት ለመምከር (1÷2-4፤ 1-12፤ 5÷7-10)፡፡
2. እምነትን ከመልካም ሥራ ለይተው የሚይዙ ሰዎች ስለነበሩ እምነት ያለ ሥራ ከንቱና የሞተ መሆኑን ለማስረዳት (1÷22፤ 2÷17-26)፡፡
3. በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚፈጸሙ የተለያዩ ስህተቶችንም ለማረም ይህቺን መልእክት ሊጽፍ ችሎአል (3÷13፤ 5÷19-20)፡፡

## የመልእክቱ አጠቃላይ ይዘት

በያዕቆብ መልእክት ውስጥ በዋናነት የሚገኘው የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ትምህርት ነው፡፡ ይህች መልእክት በስፋት የምታስተምረው ስለ ምግባር ነው፡፡ “እምነት ያለ ምግባር የሞተ ነው” በሚለው ትምህርት ላይ ተመሥርታ የእግዚአብሔር ቃል፣ የእግዚአብሐር ሕግ በተግባር መተርጐም እንዳለበት በዝርዝር ታስተምራለች፡፡ (1÷22፤ 2÷8-13) ፡፡ቃሉን ሰሚ ብቻ የሆነውን ሰው ፊቱን በመስተዋት አይቶ በኋላ የሚረሳ ሰው ይመስላል (1÷23-35) ስለዚህ በጉባኤ የሚገኙ ድሆችን መናቅ እንደማይገባ (2÷1-7) ፣ ከዚያም አያይዞ አንደበትን መግታት እንደሚገባ፤ በረከትና መርገምን በአንድ አፍ መናገር እንደማይገባ፤ በተለያዩ ምሳሌዎች ያስተምራል (1÷26፣ 3÷1-11)፡፡ ላይኛይቱን ጥበብ ከምድራዊ ጥበብ ለይቶ ይገልጻል (3÷13-18) ፡፡እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን እንደሚቃወም ለትሁታን ግን ጸጋን እንደሚሰጥ በመግለጥ ክርስቲያኖች በጌታ ፊት

ራሳቸውን እንዲያዋርዱ ይመክራል፡፡ (4÷6-16)፡፡ ክርስቲያኖች እርስ በእርስ ሊተማሙና ሊፈራረዱ አይገባም (4÷11-12)፡፡ በየዕለቱ የሚሠሩትን ሥራ ለጌታ ፈቃድ አሳልፈው መስጠት ይገባቸዋል፡፡ (4÷13-15) ፡፡

ባለጠጐች ስለፈጸሙት የተለያየ ግፍና በደል ያዕቆብ በጣም ይገስጻቸዋል (5÷1-6)፡፡ በመከራ ውስጥ የሚገኙ ወንድሞችን ደግሞ ጌታ እስኪመጣ ድረስ እንዲታገሡ ይመክራቸዋል (5÷7-9)፡፡ የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑ ነቢያትን እንዲመለከቱ በተለይም ኢዮብን ጠቅሶ በትዕግሥት እንዲጸኑ ያስተምራል (5÷10-11)፡፡ ስለ መሐላ ደግሞ በምንም ነገር መማል እንደማይገባ ጽፎአል (5÷12)፡፡ ስለ ጸሎትም ክርስቲያኖች በመከራ ጊዜ እንዲጸልዩ፤ በሕማም ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ቀሳውስትን እንዲጠሩ፤ ቀሳውስት ለታመመው ሰው ዘይት ቀብተው በእምነት እንዲጸልዩለት፤ እርስ በእርሳቸው አንዱ ለሌላው እንዲጸልዩ ያስተምራቸዋል (5÷13-16) ፡፡ የኤልያስን ጸሎት በማስረጃነት ጠቅሶ የጸሎትን ኃይል ያስረዳቸዋል (5÷16-18) ፡፡ በመጨረሻም ከእውነት የሳቱትን ኃጢአተኛ ሰዎች ከተሳሳቱበት መመለስ እንደሚገባ በማስተማር ጽሑፉን ይደመድማል (5÷19፡20)፡፡

**የመልእክቱ አከፋፈል**

የያዕቆብ መልእክት አምስት ምዕራፎች አሉት፡፡ እነዚህንም በስድስት ዐበይት ክፍሎች እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን፡፡

1. መግቢያ (1÷1)
    - ላኪውና ተቀባዮቹ (1÷1)
    - ለተቀባዮቹ የቀረበ የላኪው ሰላምታ (1÷1)
2. በእምነት ምክንያት የሚደርሰውን ፈተና ጸንቶ መታገስ እንደሚገባ (1÷2-21)
    - ፈተናውን መታገስና እንደ ሙሉ ደስታ መቁጠር እንዲገባ(1÷2-11)
    - በፈተና የሚጸና ሰው የሚያገኘው የሕይወት አክሊል (1÷12-22)
3. ስለ ምግባር የጻፈው ትምህርት እና ምክር (1÷22-2÷26)
    - ቃሉን መስማት ብቻ ሳይሆን ማድረግ እንደሚገባ (1÷22-25)
    - ስለከንቱ አምልኮና ንጹሕ የእግዚአብሐር አምልኮ (1÷26-27)
    - እውነትን በሰው ፊት በማድላት መያዝ እንደማይገባ (2÷1-7)
    - ሕግን ሁሉ መጠበቅ እንደሚገባ (2÷8-13)
    - ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ እንደሆነ (2÷14-26)
4. ከተለያዩ ስህተቶች እንዲታረሙ የጻፈው ትምህርት (3÷1-4)

- አንደበትን ከክፉ ነገር መከልከል እንደሚገባ (3÷1-12)
- ላይኛይቱን ጥበብ መያዝ እንደሚያስፈልግ (3÷13-18)
- ከትዕቢት በመራቅ ትሑት መሆን እንደሚያስፈልግ(4÷1-10)
- መተማማት እንደማይገባ (4÷11-12)
- ዕለታዊ ኑሮአቸውን ለጌታ ፈቃድ እንዲሰጡ (4÷13-17)

5. በመከራ ጊዜ ትዕግሥትና ጸሎት እንደሚያስፈልግ(5÷1-20)
   - መከራ የሚያበዙ ጨካኞችና ልባቸውን ያወፈሩ ባለጠጐች ስለሚጠብቃቸው ፍርድ (5÷1-6)
   - ስለ ትዕግሥት (5÷7-11)
   - መሓላ ተገቢ አለመሆኑ (5÷12)
   - በመከራና በሕመም ጊዜ የእምነት ጸሎት ማድረግ እንደሚገባ (5÷13-18)
6. ማጠቃለያ (5÷19-20)
   - ኃጢአተኛውን ከስህተት መመለስ እንደሚገባ (5÷19)
   - ኃጢአተኛን ከበደሉ መመለስ ከሞት ማዳን ስለመሆኑ (5÷20)

**የይሁዳ መልእክት**

ከሐዋርያት መካከል ይሁዳ የሚባሉ ሁለት ሰዎች አሉ፡፡ አንደኛው ጌታን አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ የሚባለው ነው (ሉቃ 6÷16)፡፡ የያዕቆብ ይሁዳ የሚባለው በሐዋ.ሥራ 1÷13 ላይ የያዕቆብ ልጅ ተብሎ ተጠርቶአል፡፡ በዮሐ.14÷22 ላይ ደግሞ የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳ ተብሎ ተጠርቶአል፡፡ ይህ ይሁዳ ታዴዎስ ወይም ልብድዮስ ተብሎ የሚጠራው ሐዋርያ እንደሆነ መምህራን ይናገራሉ (ማቴ.10÷3)፡፡

መልእክቲቱን የጻፈው ይሁዳ ግን የጌታ ወንድሞች ከሚባሉት አንዱ የሆነው ይሁዳ ነው፡፡ (ማቴ.13÷55)፡፡ አንዳንዶች ግን ከሐዋርያት መካከል የአስቆሮቱ ያይደለው ይሁዳ (ታዴዎስ) ነው በማለት ይናገራሉ፤ ይሁን እንጂ በመልእክቲቱ መግቢያ ላይ ጸሐፊው "የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ" ብሎ ራሱን ስለገለጠ የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ ነው (1÷1)፡፡ ምክንያቱም የአስቆሮቱ ያይደለው ይሁዳ የያዕቆብ ልጅ ተብሎአል ይሁዳ ግን የያዕቆብ ወንድም ስለሆነ የዮሴፍ ልጅ መሆኑ ግልጽ ነው (ማቴ. 13÷55) ፡፡መጽሐፈ ስንክሳርም ይህንን ሲያስረዳ "ወበዛቲ እለት ስምዐ ኮነ ቅዱስ ይሁዳ ሐዋርያ ወሰማዕት ወልደ ዮሴፍ ደራቢ ወውእቱ መምህር እምሰብአ ወክልኤቱ አርድእት" ይላል (ሐምሌ 25)፡፡ ይህም ቃል ይሁዳ ወዳል ዮሴፍ መሆኑና ቁጥሩም ከሰባ

ሁለት አርድእት መሆኑን ይገልጻል። ስንክሳር መልእክቲቱን እንደጻፋት ሲገልጽም “ወእምቅድመ ይኮንንዎ ፈነወ መልእክተ ለመሃይምናን ወይእቲ መልእክት ሳብዒት እምጽሐፈ ሐዋርያ›› ይላል። ይሁዳ በብዙ ሀገሮች እየተዘዋወረ እንዳስተማረ ስንክሳር ይናገራል። ለምሳሌ ስሟ ባልተገለጠ ስለ አንዲት ሴት ወንጌልን ከሰበከና ቤተክርስቲያን ከመሠረተ በኋላ ሮሃ ወደምትባል ሀገር እንደሔደ ይናገራል። በዚያም አውጋርዮስ የተባለውን የሮሃ ንጉሥ ከሕመሙ ፈውሶ ጥምቀተ ክርስትናን እንዳጠመቀው ይገልጣል። ከዚያም በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ አራጰ በሚባል ሀገር ገብቶ በማስተማር ብዙዎችን በክርስቶስ እንዳሳመነ ያስረዳል።

ይሁዳ በአራጰ ሀገር ወንጌልን እያስተማረ ብዙዎችን አሳምኖ ጥምቀተ ክርስትናን እያጠመቀ ቤተ ክርስቲያን እየመሠረተ መሆኑን ያወቀው የሀገሪቱ መኮንን ወይም ገዥ አስያዘውና ብዙ ሥቃይ አሰቃየው። ብዙ ምሥማር በእግሩ ላይ እንደ ጫማ ቸንክሮ የተወሰነ እርቀት እንዲሮጥ አደረገው። ከዚህም በኋላ ሰቀለውና ሞተ። (ስንክሳር ሐምሌ 23)

## የተጻፈላቸው ሰዎች

በመልእክቲቱ መግቢያ ላይ ተቀባዮቹ “በእግዚአብሔር አብ ተወደው በኢየሱስ ክርስቶስም ተጠብቀው ለተጠሩ” የሚል ቃል ይገኛል። (1÷1)። ስለዚህ በተወሰነ ቦታ እና መልእክት አይደለችም። በየትኛውም ቦታ የሚገኙ ክርስቲያኖች እንዲያነቡአት የተጻፈች አጠቃላይ መልእክት ናት።

## የተጻፈችበት ቦታና ዘመን

የይሁዳ መልእክት የተጻፈችበት ቦታ የት እንደሆነ የተመዘገበ ነገር የለም። ስለተጻፈችበት ዘመን ግን 2ኛይቱ የጴጥሮስ መልእክት ከተጻፈች በኋላ ብዙም ሳይቆይ እንደሆነ ብዙዎች ሊቃውንት ይናገራሉ። (1÷18፤ 2ኛ ጴጥ.3÷2፤ 2÷3)። ስለዚህ 2ኛይቱ በተጻፈችበት በዚያው በ68 ዓ.ም ገደማ ተጽፋለች ማለት ነው።

## የተጻፈበት ዋና ዓለማ

መልእክቷ የተጻፈችበት መሠረታዊ ዓለማ በዘመኑ ሐሰተኞች አስተማሪዎች እየበዙ መሔዳቸውን’ መሠረት አድርጎ ምእመናን ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንዲጋደሉ ሊመክር ጽፏል (ቁ.3-4)።

## የመልእክቱ አጠቃላይ ይዘት

የይሁዳ መልእክት ይዘት ከ2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ ሁለት ጋር አንድ ነው። በምእመናን መካከል ሾልከው የገቡ ሐሰተኞች ሰዎችን ክፉ ባሕርይ እየገለጠ ምእመናን በሃይማኖታቸው ጸንተው እንዲኖሩ ያሳስባል። በዚህም ውስጥ የሃይማኖት እና የሥነ ምግባር ትምህርት ይሰጣል።

የመልእክቲቱ አንባቢዎች ከዚህ ተለይተው በተቀደሰ ሃይማኖታቸው ራሳቸውን ለማነጽ መትጋት እንደሚገባቸው ይመክራል። (ቀ.20) በመንፈስ ቅዱስ እንዲጸልዩ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳቸውን እንዲጠብቁ (ቁ.21) ፤ ከተሳሳቱ ሰዎች አንዳንዶችን እንዲያድኑ ይመክራል። (ቁ.23) ። በመጨረሻም የእግዚአብሔር ጥበቃና ዕርዳታ እንደማይለያቸው ይገልጽላቸዋል። (ቁ.24) ።ይሁዳ ሐሰተኞች ተሳዳቢዎች እንደሆኑ በገለጸ ጊዜ ስድብ ተገቢ ያለመሆኑን ለማስረዳት የመላእክት አለቃ ሚካኤል ስለ ሙሴ ሥጋ በተነጋገረ ጊዜ ዲያብሎስን እንኳ "ጌታ ይገስጽህ" እንዳለው እንጂ የስድብ ቃል እንዳልተናገረው በማስረጃነት ይገልጻል። (ቁ .9) ።ይህን የጠቀሰው "ዜና ሕይወቱ ለሙሴ" (The Assumption of Moses) ከተባለው በሄኖክ የተነገረውን ትውፊታዊ ትንቢት ስለ እነዚህ ክፉ ሰዎች የተነገረ መሆኑን ገልጾ ጠቅሶታል (ቁ.14-15)።

**የመልእክቱ አከፋፈል**

በምዕራፎች ካልተከፈሉት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አንዷ የይሁዳ መልእክት ናት። መልእክቷን በአራት ክፍለን እንመለከታለን።

1. መግቢያ (ከቍ.1-3)
   - ላኪውና ተቀባዮች (ቍ.1)
   - ለተቀባዮች የቀረበ የላኪው ሰላምታ (ቍ.2)
   - መልእክቲቱን የጻፈበት ምክንያት (ቍ.3)
2. ሾልከው ስለገቡ ሐሰተኞች ክፉ ባሕርይ የሰጠው ገለጻ(ከቍ.4)
   - ክርስቶስን እንደሚክዱ (ቍ.4)
   - ስለ እነዚህ ምሳሌ የሚሆኑ፣በብሉይ ኪዳን የተፈረደባቸው ሰዎች (ከቍ.5-7)
   - የሐሰተኞቹ የምግባር ብልሽት (ከቍ.8-13)
3. ለአንባቢዎች የተላለፈ መልእክት (ከቍ.17-23)
   - የሐዋርያትን ቃል እንዲያስቡ (ቍ.17-19)
   - በሃይማኖታቸው ጸንተው ራሳቸውን እንዲጠብቁ (20-21)
   - ሌሎች ሰዎችን ከስሕተት እንዲያድኑ (ቍ.22-23)
4. ማጠቃለያ (ቍ.24-25)
   - እግዚአብሔር እንደሚጠብቃቸው (ቍ.24)
   - ይሁዳ ለእግዚአብሔር ያቀረበው ምስጋና (ቍ.25)

## ራእየ ዮሐንስ

የጥጦሰ፣ የሐሳዊመሲሕ፣ የምጸአት፣ የመንግሥተሰማያት ነገር ተገልጾለት ተናግሮታል በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኝ ብቸኛ የትንቢት መጽሐፍ ነው።

ኢትዮጰያውያን ሊቃውንት ደረቅ ሐዲስ ብለው ይጠሩታል። በውሰጡ የያዛቸው ወደ 300 የሚጠጉ ምሳሌዎችና እያንዳንዳቸው በውስጣቸው የያዙት ትርጓሜ መጽሐፉ ከሌሎች የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ልዩ ያደርጉታል።

## የመጽሐፉ ስም

በግዕዝ ራእዩ ለዮሐንስ አቡቀለምሲስ፡- በሕይወት እያለ ራእይ ያየ በአማርኛ የዮሐንስ ራእይ በግሪኩ አፓካሊርሂሊስ ማለት መግለጥ፣ የተሸሸገውን ማሳወቅ ማለት ነው በእንግሊዝኛ ሪቨሌሽን ተብሎ ይጠራል።

## የመጽሐፉ ጠቀሜታ /ዓላማ/

1. የእግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር የተገለጠበት መጽሐፍ ነው።
2. በተስፋ የተሞላ መጽሐፍ ነው፡- የቅዱሳንን ዕንባ እንደሚአበስ
3. የድል መጽሐፍ ነው፡- በመጨረሻ ዲያብሎስን እንዴት ድል እንደሚአደርገው ይናገራል።
4. በመንፈስ የሚፈጸምን ሥርዓተአምልኮ የሚአሳይ መጽሐፍ ነው
5. የመንግሥተሰማያት መግለጫ መጽሐፍ ነው
6. የሰውን ፍጹም ድህነት የሚያሳይ መጸሐፈ ነው

## መጽሐፉን የጻፈው ማነው?

ራእየ ዮሐንስን የጻፈው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው።

ሊቃውንት መጽሐፉን ዮሐንስ ወንጌላዊ ለመጻፍያስቀመጧቸው መስረጃዎች

1. የመጽሐፉ ጸሐፊ የታናሽ እስያ አብያተክርስቲያናትን የሚያውቅና በአካባቢው ያገለገለ መሆኑን ራእዩ የስረዳል
2. በድምጥያኖስ ዘመነመንግሥት ወንጌላዊ ዮሐንስ ወደፍጥሞ ደሴት ተግዞ እንደነበርና በዚያም ራእዩን እንዳየ /ራእይ 1፡9/ የቤተክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል፡፡
3. ምንም እንኳ በወንጌሉና በራእዩ መካከል ልዩነት ቢኖርም ሁለቱን መጻሐፍት ብቻ የሚአመሳስሏቸው ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በግ፣ ቃል፣ ድል፣ እውነት የሚሉት በሁለቱም መጻሕፍት ተደጋግመው ተገልጠዋል፡፡
4. ስሙን ገልጦ የተናገረበት ቦታ ስላለ ለምሳሌ
   - ለባሪያው ለዮሐንስ /ራእ. 1፡1/
   - እኔ ወንድማችሁ የሆንኩ ከእናንተም ጋር አብሬ የኢየሱስ ክርስቶስን ትዕግስት የምካፈል /ራእይ. 1፡9/ ያለውንና ሌሎች ተመሳሳይ ሀሳቦችን በማንሳት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ራእዩ የዮሐንስ ወንጌላዊ መሆኑን በትርጎሜአቸው አስረድተዋል፡፡

**የት ተጻፈ?**

ወንጌላዊው ዮሐንስ በመጽሐፏ እንደገለጠልን /ራእ. 1፡9/ ራእዩን ያየውም የጻፈውም በፍጥሞ ደሴት ነው፡፡

**መቸ ተጻፈ?**

ቅዱስ ዮሐንሰ በድምጥያኖስ ዘመን በተነሣው የክርስቲያኖች ስደት ተግዞ ከኢየሩሳሌም ጥፋት በኋላ በ95/96 አካባቢ ራእዩን እያየ የጻፈ መሆኑን ብዙዎቹ ሊቃውንት ተስማምተውበታል፡፡

**ለማን ተጻፈ?**

ራእዩ የተጻፈው በቅዱስ ዮሐንስ ሀገረ ስብከት ውስጥ ሥር ለነበሩት ለሰባቱ የታናሽ እስያ አብያተክርስቲያናት ነው፡፡ ራእ. 1፡11

አጠቃላይ መልእክቱ Zስት ክፍሎች እንዳሉት ይታያል፡፡

ምዕራፍ አንድ መግቢያ ነው፡- ማለት ራእዩን ማን እንደገለጠው ለማን እንደተገለጠ፣ መልእክቱ ለነማን እንደሚላክ ራእዩ የት ቦታ እንደታየ ባጭሩ ይገልጻል፡፡

ከምእራፍ 2-3 በታናሽ እስያ ለሚገኙት ለሰባቱ አብያተክርስቲያናት በየራሳቸው የተላከላቸውን መልእክት ይዟል፡፡

ከምእራፍ 4-22 ለመላው ዓለም የተገለጠ መልእክተ ነው በተለይ ደግሞ ሐሳዌመሲሕ በሚነሣ ጊዜ ቤተክርስቲያን የሚደርስባትን ፈተና እና የመውጫውንም መንገድ ጽኑዐንም /ቅዱሳን/ የሚያገኙትንም ዋጋ ይተነትናል፡፡

## የራእየዮሐንስ ልዩ መገለጫዎች

1. በምሳሌዎችና ምልክቶች የተሞላ ነው

   ራእዩ ጥልቅ ምሥጢርን የያዘ በመሆኑ ትርሙም ጥልቅና ሰፊ በመሆኑ ብዙ ምሳሌዎችና መልክቶች ተገልጠዋል፡፡

2. የሁለት ዓለም መጽሐፍ ይባላል

   ዮሐንስ በራእዩ ፍጥሞ በምትባል ደሴት በመንፈስ ነበርኩ በማለት የገለጠውን በመያዝ ሊቃውንት ፍጥሞ ደሴት የተባለች ክርሰቲያኖች ዝግጅት የሚአደርጉባት ይህች ዓለም ስትሆን በመንፈስ ነበርኩ ማለት ደግሞ ሰማያዊውን ሕይወታቸውን ያሳያል፡፡

3. ዙፋን፡- በመጽሐፍ ውስጥ ዙፋን የሚለው ቃል 40 ጊዜ ያህል ተደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡

   ይህም ክርስቲያኖች መከራውን ሁሉ ታግሰው እስከመጨረሻው ቢጸኑ የሚያገኙትን ክብርና የኢየሱስ ክርስቶስን ዘለዓለማዊ ሰልጣን ያስረዳል፡፡

4. የፍቅር አምላክ መሆኑን

   መጽሐፉን ሲጀምር በ3ኛው ምዕራፍ በአንተፊት የተከፈተ በር ሰጥቸሀለሁ ማንም ሊዘጋው አይችልም ይላል ራእ. 3፡8

   እነሆ በደጅ ቁሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደእርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ ራእ. 3፡20 የሚለው ተስፋ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅር የሚአመለክት ነው

## ሰባት ቁጥር በራእየዮሐንስ

በዮሐንስ ራእይ ተደጋግመው ከተገለጡት ነገሮች አንዱ 7 ቁጥር ነው

1. ሰባቱ አብያተክርስቲያናት /ራእ. 1፡4፤1/ እነዚህ አብያተክርስቲያናት በ7ቱ መቅረዞች ተመስለዋል/ራፍ. 1፤12፤20/ ይህም 7 ቁጥር የፍጹምነት ማረጋገጫ ስለሆነ መልእክቱ ቤተክርስቲያንን ለፍጹም ክብር ለማብቃት የተላከ መሆኑን ከመግለጡም በላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የማይጠፋ ብርሃን ሁና በውስጧ እንደሚአበራና የጨለማውን ዘመንም እንደሚያሻግራት ያመለክታል፡፡
2. ሰባቱ መንፈሶች /ራእ. 1፡4/ አንዳንድ ሊቃውንት ሰባቱ መንፈሶች ሰባቱ ሊቃነመላእክት ናቸው ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ የመንፈሰ ቅዱስን ፍጹም የሆነ ሀብት /ሥራ/ የሚአመለክት ነው ብለው ተርጉመዋል፡፡
3. ሰባቱ የእሳት መብራቶች የሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርሰቲያን ናቸው፡፡ ሌላው መንፈስ ቅዱስ ለሰው የሚሰጠው ፍጹም ሀብቱ ነው /ራእ. 5፡1

4. ሰባቱ ቀንዶች /ራእ.5፡6/ ዮሐንስ በራእዩ በዙፋኑ ላይ ያየው በግ ሰባት ቀንዶች ነበሩት፡፡ ቀንድ የኃይል፣ የክብር፣ የስልጣን ምሳሌ ነው፡፡ በሥጋ ደካማ መስሎ የተገለጠው አማናዊ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ዲያብሎስን ድል ያደረገበት ኃይል የባሐርይው /ገንዘቡ/ እንደሆነ ያመለክታል
5. ሰባት ዓይኖች /5፡6/ ወልደአምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ማእምረ ኩሉ፣ ማእምረኅቡዓት መሆኑን ያመለክታል፡፡
6. ሰባት ሽ ሰማዕታት /ሪእ. 11፡13/ ሁለቱ ነቢያት ኤልያስና ሄኖክ የሚሰጡትን ምስክርነት ሰምተው በማመናቸው በሐሳዌመስሕ የሚሰውትን ሰማዕታት በፍጹም ቁጥሮ እንዲህ አለ፡፡
7. ሰባት እራሶች /ራእ.12፡3/ የተነሣው አውሬ ሰባት እራሶች የሉት መሆኑ ከዚያ በፊት ታይቶ፣ ተሰምቶ የማያውቅ ፍጹምና አሰቃቂ መከራ በቤተክርስቲያን ማምጣቱን መናገር ነው፡፡
8. ሰባት ተራሮች /ራዕ.17፡9/ አመነዝራዋ ባቢሎን የተቀመጠችባቸው ተራራዎች ሰባት ናቸው፡፡ ይህም አያሌ የዓለም መሪዎችንና ኃያላን ሀገሮችን የሚአስከትለው የሐሳዌመሲሕ መንግሥት ነው፡፡

**የመጽሐፉ አከፋፈል**

ራእየዮሐንስ በዘጠኝ ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡

1. መግቢያ ራእ፡1-20
2. ለሰባቱ አብያተክርስቲያናት የተጻፉ መለእክቶች ራእ.2 እና 3
3. ሰባቱ ማኅተሞች /4፡1-8፡5/
4. ሰባቱ መለከቶች /8፡6-11፡18
5. የዓለም ክፉ ዘመናት /11፡19፡14፡20/
6. ሰባቱ መቅሰፍቶች /15፡1-16፡21/
7. ባቢሎንና አርማጌዶን /17፡1-19፡21/
8. የሺ ዓመት መንግሠትና የመጨረሻው ፍርድ /20፡1-22፡5/
9. ማጠቃለያ /22፡6-21/

ራእየዮሐንስን በምልዐት ማወቅ የሚቻለው በዓለም ፍጻሜ ብቻ ነው

ሪእየዮሐንስ የብዙ ተስፋዎች መጽሐፍ ነው ለምሳሌ

- የተከፈተ የገነት በር
- የማታልፍ መንግሥት
- ሰማያዊ መዝሙር

- የበጉ ሠርግ
- አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር
- ዘንባባ ይዞ ማመስገን
- እንባቸውን ያብሳል
- ከበጉ ጋር በጽዮን ይነግሣሉ
- የታረደው በግ ድል አድራጊነት
- የዲያብሎስ ድል መሆንና ወደጥልቁ መጣል የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

**ምዕራፍ 1**

በዚህ ምዕራፍ ዮሐንስ የኢየሱሱ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት ማለትም፡- ቀዳማዊነቱን፣ ማእከላዊነቱንና፣ ደኃራዊነቱን ይጽፍና ከዚህም በተጨማሪ ዳግም ምጽአቱን ይጸፋል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ራእዩ የትና እንዴት እንደተገለጠለት ይጽፋል ይህንንም ራእይ ለ7ቱ አብያተክርስቲያናት ጻፍ ተብሎ እንደታዘዘ ይጽፋል፡፡

**ምዕራፍ አንድ 20 ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡም**

1. የነበረው፣ ያለው ዳግመኛ የሚመጣው በማለት ዘለዓለማዊነቱን እና ፈራጅነቱን ይናገራል፡፡
2. ስለሰባቱ መናፍስት፡- ይኸውም 7ቱ ሊቃነመላእክት፣ የመንፈስ ቅዱስ ፍጹም ሀብት፣ ተብሎ ተተርጉሟል፡፡
3. የሙታን በኩር ይለዋል ይኸውም ሞትን ድል አድርጐ ስለተነሣ
4. የነገሥታት ገዥ ብሎታል ይኸውም ነገሥታትን ከመቃብር አስነሥቶ የሚገዛ ዘለዓለማዊ ንጉሥ መሆኑን ያስረዳል፡፡
5. ካህናት አንድንሆን ላደረገን ይላል፡፡ ከህነት ሁለት አይነት ነው፡፡

   አንደኛው በመመረጥና በመሾም የሚገኝ ሲሆን

   ሁለተኛው ደግሞ በጥምቀት የሚገኝ የልጅነት አገልግሎት ነው
6. ከደመና ጋር ይመጣል ሲል፡-
   - በባሕርይ ክብሩ ሲሆን
   - በሥጋማርያም / በክበብ ትስብእት/
7. አልፋና ኦሜጋ ይለዋል፡-
   - አንድነት Zስትነት ገንዘቤ የሚሆን
   - አ.ል.ፋ. /ምህጻረ ቃል ሁኖ አ ማለት እግዚአብሔር አብ ል ማለት እግዚአብሔር ወልድ ፋ ማለት ደግሞ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው
8. የጌታ ቀን ያላት ዕለተ እሁድ ናት ብለው መምህራን ተርጉመዋል

9. 7ቱ የወርቅ መቀረዞች፡- ፈትሉ የሰውነታቸው፣ ወርቁ የንጽህናቸው እሳቱ የመከራቸው፣ ብርሃኑ የጸጋቸው ምሳሌ ነው፡፡

10. በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ፡- ዮሐንስ ጌታን በራእይ ሲመለከተው በወርቅ መታጠቂያ ታጥቆ ነው ይኸውም ነጹሀባሕርይ መሆኑን መታጠቁ ትእምርተኃይል፣ ትእምርተተልእኮ፣ ተዋሕዶን ገንዘብ ማድረጉን መናገር ነው

11. ጠጉሩ እንደነጭ የበግ ጠጉር የሆነ ማለት ብሉየመዋዕል፣ ጽሩየ ባሕርይ መሆኑን ያስረዳል

12. ዓይኖቹ እንደእሳት ነበልባል ናቸው ሲል
    - ፍጥረታታን የሚአውቅ የሚጠብቅ ማለት ሲሆን
    - ዓይኖቹ የተባሉ ነቢያት፣ እግሮቹ የተባሉ ሐዋርያት፣ ቀሳውስተ፣ ዲያቆናት ናቸው

13. እግሮቹ የጋለ/የነጠረ/ ናሰ ይመስላሉ ሲል ትእምርተ መዓት ትእምርተ በቀል ገንዘቡ የባሕርይው የሆነ ማለት ነው፡፡ ሌላው እግሮቹ የተባሉ ብሉይና ሐዲስ ናቸው፡፡

14. በቀኝ እጁ 7ቱ ከዋክብት ነበሩ ማለት 7ቱ ኤጲስ ቆጶሳት በስልጣኑ ይጠበቃሉ ማለት ነው፡፡

15. ከአፉ በሁለት ወገን የተሰለ ስለታም ሰይፍ ወጣ ማለት ንዑና ሁሩ የሚልበት ስልጣን የባሐርይው ነው ማለት ነው፡፡

16. ፊቱ እንደሚአበራ ፀሐይ ነበር፡- ማለት ፀሐይ 3 ነገር አላት ክበብ፣ ብርሃን፣ ሙቀት በክበቡ አብ፣ በብርሃኑ ወልድ፣ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል፡፡ ስለዚህ አንድነት Zሰትነት ገንዘቡ የሚሆን ተብሎ ይተረጐማል፡፡

17. የሞትና የሲኦል መክፈቻ አለኝ ሲል
    - ሞትን ፣ መቃብርን የማሳልፍበት ስልጣን ገንዘቤ ነው፡፡
    - ሙቸ፣ ተቀብሬ ሞትን ድል አድርጌ ተነሥቻለሁ ሲል እንዲህ አለ፡፡

**ምዕራፍ 2 እና ምዕራፍ 3**

እነዚህ ምእራፎች በዮሐንስ አማካኝነት በሰባቱ የታናሽ እስያ አብያተክርስቲያናት በኩል በመላው ዓለም መልታ ለምትገኘው ቤተክርሰቲያን እግዚአብሔር የገለጠውን ምስጢር እናያለን፡፡

እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ጠንካራና ደካማ ጐን ነበረው የበረታው እንዲቀጥል ከድካሙ እንዲነጻ መልእክት ተልኰለታል፡፡ በዚህም መሠረት ስማቸውን በማስቀደም ጠንካራ ጐናቸው ደካማ ጐናቸው፣ መፍትሔው ፣ በዝርዝር ተቀምጧል፡፡

1. የኤፌሶን አለቃ ስሙ አርስጦን ደካማ ጐኑ የቀደመ ፍቅሩን መተው
2. የሴሜርኔስ አለቃ ስሙ ኄሬኔዎስ እስከሞት ድረስ የታመንክ ሁን
3. የጴርጋሞን አለቃ ስሙ ጋይዮስ የኒቆላውያንን ትምህርት የያዙ ሰዎች ባንተዘንድ አሉ
4. የትያጥሮን አለቃ ስሙ ሉክዮስ ኤልዛቤልን ዝም ብለሀታልና

**ምዕራፍ 3**

5. የሰርዴሲሶን አለቃ ስሙ አርስጦን ስምህ ህየው ነው አንተግን ሙተሀል
6. የፊልድልፊልያ አለቀ ስሙ ድሜጥሮስ አክሊልህን/ ክብርህን/ ማንም እንዳይወስድብህ ያለህን አጽንተህ ያዝ
7. የሎደቅያ አለቃ አረክቦስ በራድ ወይመ ትኩስ አይደለህምና

**ምዕራፍ 4**

**ከዚህ ቀጥለው የሉ ምእራፎች ዮሐንስ በራእዩ ስለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስለመንግሥተሰማያትና በመጨረሻው ዘመን በቤተክርስቲያን ላይ ስለማደርሰው ፈተና ያያቸው ናቸው፡፡**

እነዚህ ራዕዮች 3ቱን የቤተክርስቲያን የጉዞ ምዕራፎች የሚአሳዩ Zስት ተከታታይ ራእዮች ናቸው፡፡

1. 7ቱ ማንተሞች፡- እነዚህ ቤተክርስቱያን የሚአጋጥማትን ፈተና እና የታረደው በግ የሚአደርግለትን ጥበቃ እና መግቦት የሚአመለክቱ ናቸው
2. 7ቱ መለከቶች፡- እነዚህ ዓለም በንስሐ እንድትመለስ እግዚአብሐር የላካቸው መንቂያ ማስጠንቀቂያ ናቸው
3. 7ቱ መቅሰፍቶች፡- እነዚህ ደግሞ እግዚአብሔር በሰጣቸው ማስጠንቀቂያ አልመለስ ብለው ልባቸውን ያደነደኑትን ለመቅጣት ያመጣቸው ቁጣዎችና መዓቶች ናቸው፡፡

ምዕራፍ አራት አስራ አንድ ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡም

1. በሰማይ የተከፈተ በር፡- ማለት በሰማይ መዘጋት መከፈት ኑሮ ሳይሆን የልታወቀ ምስጢር ተገለጠ ይኸውም የ4ቱ ኪሩቤልና የ24ቱ ካህናተሰማይ ሁኔታ ታወቀ ማለት ነው፡፡
2. ዕንቈ ኢያስጲድና ሰርዲኖ፡- የከበሩ ደንጋዮች ናቸው ጽርየተባሕርዩን መናገር ነው፡፡
3. የወርቅ አክሊል ደፍተዋል፡- ማለተ ክብራቸውን መናገር ነው
4. የብርጭቆና የበረድ ባሕር፡- ይህም ማለት ሰው ሁሉ አምኖ በጥምቀት ከብሮ የመኖሩ ምሳሌ፡፡
5. ነጭ ልብስ ለብሰዋል፡- ማለት ጸጋቸውን ንጽህናቸውን መናገር ነው
6. ዓይንን የተሞሉ ናቸው፡- ማለት ኃላፍያትንና መጻዕያትን/ ያለፈውንና የሚመጣውን ነገር ሁሉ ያውቃሉ ማለት ነው፡፡

**ምዕራፍ 5**

**ምዕራፍ 5፡14 ቁጥሮች ያሉት ሲሆን በውስጡም**

1. በውስጥ በአፍአ የተጻፈባት፡- ማለት ከምጽአት በፊትና ከምጽአት በኋላ የሚደረገው/የሚፈጸመው/ ነገር ሁሉ እንደተገለጠለት ያስረዳል
2. በሰባቱ ማህተም የተዘጋ፡- ማለት ምስጢረ ምጽአት የሚፈጸው ሁሉም ነገር ከሆነ ከተፈጸመ በኋላ እንደሆነ ሲአስረዳው ነው፡፡
3. ሞዐ አንበሣ ዘእምነገደ ይሁዳ፡- የተባለ ከቤተይሁዳ የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን መስዋዕት በመሆኑ በግ ተብሎ ሲጠራ ድል በማድረጉ ደግሞ አንበሣ ተብሎ ተጠርተል፡፡
4. 7 ቀንዶችና ሰባት ዓይኖች ነበሩት ሲል ፍጹም የሆነ ስለጣን ያለው ሲሆን ቀንደች ዓይኖች የተባሉ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ቀሳውስት ዲየቆናት ናቸው፡፡
5. ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረካቸው፣ በምድር ላይ ይነግሣሉ ማለት አማልክተ ዘበጸጋ ይባላሉ ማለት ነው፡፡
6. አዲስ ቅኔ ይዘምራሉ ማለት፡- ስብሐት ለእግዚአብሐር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ እያሉ የመሰግናሉ ማለት ነው፡፡

**ምዕራፍ 6**

**ምዕራፍ ስድስት አስራ ሰባት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፡-**

1. ፈረስ ፀዐዳ/አምባላይ ፈረሰ፡- በዚህ የተመሰለ የሐሳዌ መሲሕ ዘመን ነው፡፡ አይሁድ ነግሮላቸው ደስ ብሏቸዋልና ፀዐዳ አለው፡፡ ሌላው ደግሞ ምእመናን መከራ ተቀብለው መንግሥተሰማይን ወርሰውበታልና የሐሳዊመሲሕን ዘመን ፀዐዳ አለው፡፡
2. ፈረስ ቀይሀ/ዳማ ፈረስ፡- የተባለ ዘመነሐሳዌመሲሕ ነው የምእመናንን ደም ያፈሳልና፡፡ ሌላው የጌታ ሰው መሆን ቀይህ አለው ወቀይህ በትስብእቱ ይለዋልና፡፡
3. ፈረስ ጸሊም/ጉራቻ ፈረስ/ የሐሳዊመሲሕ ዘመን ነው በዘመኑ ረኃብ ችግር ሁኗልና፡፡ ሌላው ጸሊም ያለው የጌታን ሰው መሆን ነው፡፡ ምክንያቱም ሰው ሲሆን ሰው የሆነበትን ሁኔታ የሚአውቅ የለምና፡፡ እንዘሰብእ፡ ሂ መኑ ይክል ያእምሮ
4. ፈረስ ሐመልሚል/ሐመር/ሰራን/ቅጥልጣል ይለዋል ፈጣን ለማለት ነው፡፡ በዚህም የተመሰለ የሐሳዊመሲሕ ዘመን ነው አምላክ ወስብእ ነኝ የላልና ሌላው ሐመልሚል የተባለ ጌታ ነው አምላክ ወሰብእ ነውና፡፡

**ምዕራፍ 7**

**ይህ ምዕራፍ አስራ ሰባት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፡-**

1. አራቱ ነፋሳት የእግዚአብሐር ፍርድ፡- ኀልፈተዓለም መሆኑን ያሳየዋል

2. አንድመቶ አርባ አራት ሺ፡- የታተሙ ሰዎች ቁጥር ጠቅላላ ያመኑ፣ የተጠመቁ ምእመናን ቁጥር ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ኤፌ.4፡3 ላይ ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ ይላል፡፡ ዳግመኛም ያተመን የመንፈሱንም መያ በልባችን የሰጠን እግዚአብሔር ነው ይላል 1ኛ ቆሮ. 1፡22
3. ነጭ ልብስ ለብሰዋል ማለት ክብራቸውን መናገር ነው፡፡
4. የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘዋል ማለት የድል አድራጊነት ምልክት ነው፡፡
5. ልብሳቸውን አጥበው በበጉ ደም አነጹ ማለት በጥምቀት፣ በንስሐ ከበሩ
6. ወደሕይወት ውኃ ምንጭ ይመራቸዋል ማለት በልጅነት ያገኙት ክብር ነው
7. እንባቸውን ከዓይናቸው ያብሳል ማለት ፈጽሞ ደስ ያሰኛቸዋል ማለት ነው፡፡

## ምዕራፍ 8

### ምዕራፍ አሰራ Zስት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡም

1. እኩለ ሰዓት የሚአህል ዝምታ ሆነ ማለት ዘለዓለማዊ እረፈትእንዳለ ያሳየዋል፡፡
2. መለከት፡- አዋጅ ትዕዛዝ ተብሎ ይተረጐማል
3. ደም የተቀላቀለበት በረዶና እሳት ማለት በኃጥአን ላይ የታዘዘውን መቅሰፍት መናገር ነው፡፡
4. ተራራ የተባሉ ነገሥታቱ፣ መርከቦች የተባሉ መምህራን፣ ተላቅ ኮከብ የተባለ ዲያብሎስ፣ ንስር የተባለ መልአኩ ነው፡፡

## ምዕራፍ 9

### ምዕራፍz ሃያ አንድ ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ

1. የጥልቁን ጉድጓድ የሚከፍትበት ቁልፍ የሰበድአትን ከተማ የሚከፍትበት ማለት ሲሆን ሰበድአት ማለት ህብረብዙ ማለት ነው፡፡
2. ብዙ ጢስ ሲወጣ አየሁ፡- ማለት የሠራዊቱን ብዛት፣ የሚሰራውን ክህደት ኑፋቄ ብዛት መናገር ነው፡፡
3. ማህተመ እግዚአብሔር፡- ማለት ደመማህተሙ ማለት ነው፡፡
4. አምስት ወር፡- መንፈቁ 6 ሲሆን 5 ያለበት ምክንያት አንዱ መጡ ቀሩ አየተባሉ የቆዩበት፣ ሌላው የ5ቱ ህዋሳት መሳሌ ነው፡፡
5. በኤፍራጥስ ወንዝ ተግዘው ያሉ አራቱ መላእክት፡- የተባሉ በኖz ዘመን በኖz ጸሎት አማካኝነት እስከመጨረሻው ዘመን የታሰሩ እነዚህ በሐሳዌ መሲሕ ጊዜ ተፈተው ሕዝቡን ያስታሉ፡፡

## ምዕራፍ አስር

## መዕራፉ አስራ አንድ ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ

1. ከሰማይ የወረደ ግሩም መልአክ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሰማያዊ መሆኑንና ልጆቹን ለሰማያዋ ክብር የሚአበቃ ስለሆነ እንዲህ አለ
2. ቀስተደመና ተጐናጽፎ፡- ማለት የባሕርይ ክብሩን ገንዘብ አድርጐ ማለት ነው።
3. እግሮቹ እንደእሳት አምዶች ናቸው፡- ሲል ኃይሉን፣ ብርቱነቱን/ትእምርተ መዓት/ ገንዘቡ መሆኑን ያስረዳል።
4. የተከፈተች ትንሽ መጽሐፍ፡- ማለት ምስጢረ ምጽአቱ በቃሉ ትነገራለች ማለት ነው።
5. አንድ እግሩን በየብስ፣ አንድ እግሩን በባሕር ላይ ሁኖ መታየቱ የየብስም የባሕርም አምላክ ነኝ ሲል ነው።
6. እንደአንበሣ ሲአገሳ መታየቱ፡- ቤተክርስቲያንን መርዳቱንና አጋንንትን ድል ማድረጉን ያስረዳል።
7. በማzተም ዝጋው አትጻፈው አለኝ፡- ሲል ጊዜው አለመድረሱን ያስረዳል
8. ውሰድና ብላት ማለት ምስጢረ ምጽአትን እወቃት ማለት ነው

## ምዕራፍ 11

## ምዕራፍ አስራ አንድ አሰራ ዘጠኝ ቁጥሮች ያሉት ሲሆን በውስጡ፡-

1. የተለካ የተሰፈረ ቤተመቅደስ፡- የተባለ የምእመናን ሕይወት ነው። ትን ሕዝ 40፡48፣ ከ30 ጊዜ በላይ ለክቷል።
2. ውድሞው በውጭ ያለው ለአሕዛብ ተሰጠ ማለት፡- የአሕዛብን ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ተሰጠ ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎ 2፡4 ላይ ይነብር ቤተመቅደስ/ቤተእግዚአብሔር/ ይላል ከዚህ እንዳልገባ ዮሐንሰ ይናገራል። እንደምን ነው ቢሉ ቅዱስ ጳውሎስ ቤተእግዚአብሔር ያለው ስመ እግዚአብሔር የሚጠራበትን የካህናቱን ቤት ነው እንጅ ነገር እንደዮሐንስ ነው ቤተእግዚአብሔር አልገባም።
3. አርባ ሁለት ወር፡- ያለው የሐሳዊመሲሕን ዘመነ መንግሥት ነው ትን ዳን ምዕ. 8 ላይ 2300 ቀናት ብሎታል Zስት ዓመት ከ6 ወር ማለት ነው
4. ማቅ የለበሱ ሁለቱ ምስክሮች የተባሉ፡- ኤልየስና ሄኖክ ናቸው። ሚል.4፡5 ፣ ዘፍ.5፡24። ዕፀዘይት፣ መቅረዞች ማለቱ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙ የእግዚአብሐረ ባለሟሎች ለማለት ነው።
5. የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ ማለት፡- መንግሥተ ሰማያት ተሰጠች ማለት ነው። የመቅደሱ ታቦት ታየ ማለት፡- ህጉን የጠበቀች ምእመን ከብራ ታየች ማለት ነው።

6. መብረቅ ነጐድጓድ ሆነ ማለት፡- መቅሰፍተኃጥአን ታዘዘ፣ ህልፈተ ዓለም ሆነ ማለት ነው።

**ምዕራፈ 12**

**ምዕራፍ አስራ ስምንት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ**

1. ፀሐይን የተጐናጸፈችው ሴት የተባለች፡-
    - ቤተክርስቲያን ስትሆን
    - እመቤታችን ናት ብለው መምህራን ተርጉመዋል
2. ዘንዶው የተባለ ዲያብሎስ ነው። ዮሐንስ ዲያብሎስን ዘንዶ፣ አውሬ የቀደመው እባብ በማለት ይገልጸዋል።
3. 7ቱ እራሶች የተባሉ 7ቱ አርእስተኃጣውእ ሲሆኑ አስር ቀንዶች የተባሉ አላማውን የሚአስፈጽሙለት አስሩ ነገሠታት ናቸው
4. የሰማይን ከዋክብት እየሳበ ወደምድር ጣላቸው፡- የተባሉ ዲያብሎስ በወደቀ ጊዜ ከአርሱ ጋር ወደጥልቁ የተጣሉት አጋንንት ናቸው።
5. 1260 ቀናት የተባሉ 3 ዐመት ከ6 ወር የሐሳዌ መሲህ ዘመነ መንግሥት ወይም ኤልያስና ሄኖክ በዚህ ዓለም የሚአስተምሩበት ዘመን ነው።
6. ለሴቲቱ የተሰጧት ሁለቱ ክንፎች፡- ለምእመናን/ለቤተክርስቲያን / ምግባር ከሀይማኖት ሃይማኖት ከምግባር ሲሆን ለእመቤታችን ደግሞ ንጽሀሥጋ ንጸሀነፍስ ነው። ተብሎ ተተርጉሟል

**ምዕራፍ 13**

**ምዕራ፭ አስራ ስምንት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ**

1. አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ ሲል አውሬ የተባለ ሐሳዌመሲሕ ነው ከባሕር ሲወጣ ማየቱ መንግሥቱ ገና ስላልተደላደለ ነው።
2. አስር ቀንዶች ሰባት እራሶች አሉት ማለት 7ቱ እራሶች 1ኛ 7ቱ አርስተኃጣውእ ናቸው

    እነሱም፡- - ኀጢአተአዳም - ኃጢአተ እስራኤል
    - ቅትለተ አቤል - ቅትለተ ዘካርያስ
    - ጥቅመ ሰናፆር - ሞተወልደ እግዚአብሔር ናቸው
    - ኃጢአተሰዶም እነዚህ ሁሉ በእርሱዘመን ይሰራሉና ነው። ሌላው 7 ራሶች የተባሉ 7ቱ ሀገሮች ናቸው እነሱም ፋርስ ባቢሎን፣ ፅርዕ፣ ሜዶን፣ ግብፅ፣ ኢየሩሳሌምና ሮም ናቸው።

3. የስድብ ስም አለበት ማለት አምላክ ነኝ ይላልና ነብር ይመስላል ማለት መንግሥተፋርሰ ገንዘቤ ነው ይላልና እግሩ እንደድብ ነው ማለት ድብ ከጅብና ከአንበሣ የሚወለድ እንስሳ ነው እሱም መነገሥተዳርዮስ ገንዘቤ ነው ይላልና፡፡
4. አንዲቱ በሞት አወጋግ የተወጋች ናተ ቁስሉም ዳነ ማለት ኃጢአተ አዳም በሞተወልደ እግዚአብሔር ጠፍታ በሱ ጊዜ ትሰራለችና አንዲህ አለ፡፡
5. ሌላ አውሬ ከየብስ ወጣ የተባለ፡- ሐሳዌሌልያስ ነው፡፡ ሁለት ቀንዶች የተባሉ ሐሳዌሌልያስና ሕሳዌ አብድዩ ናቸው፡፡
6. 666 የሚለው ቁጥር፡- እንደማንኛውም ሰው 666 አስራው ያሉት ፍጡር መሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡

**ምዕራፍ 14**

**ምዕራፀ ሃያ ቁጥሮች ሲኖሩት በውሰጡም፡-**

1. በጉ በደብረጽዮን ቁሞ አየሁ ማለተ፡- በመስቀል ተሰቅሎ፣ ጠላቱን ድል አድርጐ ማየቱንና ምስጢረ ምጽአቱም የሚፈጸም በዚያ ነውና አንደህ አለ፡፡
2. አስራ አራት እልፍ ከአራትሽ ህጻናት የተባሉ፡- በሰማዕትነት የሚሞቱትን በፍጹም ቆጥሮ እና በኄሮድስ ጊዜ የሞቱት ህጻናት ናቸው
3. እንግዳ ምስጋና የተባለ፡- ሰው አምላክ ሆነ፣ አመላክ ሰው ሆነ ያለው
4. ሌላ ሁለተኛ መልአክ የተባለ፡- ጌታ ነው፡፡ ኤልያስ፣ ዮሐንስ መጥምቅ ነው የሚሉም አሉ፡፡
5. ሁለተኛ መለአክ ተከተለው ያለው፡- ሄኖክ፣ ሐዋርያት ናቸው
6. Zስተኛ መልአክ የተባለ፡- መጻሐፍት፣ እስከምጽአት የሚነሡ መምህራን ናቸው፡፡
7. ስለታም ማጭድ የተባለ፡- ዓለምን የሚአሳልፍበት ስልጣን ነው፡፡

**ምዕራፍ 15**

**ምዕራፀ ስምንት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፡-**

1. ሞየምትመስል ባህር የተባለች፡- መንግስተሰማያት ናት እመቤታችንም የሚሉ አሉ
2. እሳት የተቀላቀለባት፡- መለት የሚቀበሉት መከራና የሚአገኙት ክብር ነው፡፡
3. በሰማይ ያለ መቅደስ ተከፈተ ማለት፡- የልታወቀ ምስጢር ተገለጠ ማለት ነው፡፡
4. ብሩህ ልብስ ለብሰዋል ማለት ፀጋቸውን መናገር ነው
5. የወርቅ ዝናር ታጥቀዋል ማለት፡- በንጽህና ሁነው የሚሰጡት አገልግሎት /ምስጋና/ ምሳሌ ነው፡፡

**ምዕራፈ 16**

**7ቱ መቅሠፍታት**

ይህ ምዕራፍ ሃያ አንድ ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ

1. የመጀመሪያው መልአክ ጽዋውን በምድር ላይ አፈሰሰ ማለት በአይሁ ላይ የሚመጣውን መከራ መናገር ነው በምድር ማለቱ እስራኤል ዘሥጋ ናቸውና
2. ሁለተኛው በባሕር ላይ ማለት፡- አሕዛብ ናቸው
3. Zስተኛው በአፍላግ ፣ በአንቅዕት ላይ አፈሰሰ ማለት፡- ሐሰተኞች መምህራን የማአስተምሯቸው ኑፋቄዎች ፍልስፍናዎች ናቸው፡፡ ደም መሆኑ ተከታዮቹ በሙሉ ለሞት መብቃታቸው ነው፡፡
4. አራተኛው ጽዋውን ወደፀሐይ አፈሰሰ ማለት፡- መምህራነ ወንጌል ካህናት ናቸው፡1 መሞታቸውን መናገር ነው፡፡
5. አምስተኛው በሐሳዌመሲሕ ከተማ አፈሰሰ ማለት፡- ኃይሉ እየደከመ መሄዱን መናገር ነው፡፡
6. ስድስተኛው በኤፍራጥስ ወንዝ ከወደ ምስራቅ የሚመጡ ነገሥታት መንገዳቸው ጥርጊያ ትሆን ዘንድ ማለት ብሐረብፁዐን ያሉ ሰዎች በመጨረሻ ዘመን እንደሚመጡ መናገር ነው፡፡
7. ሰባተኛው ጽዋውን በነፋስ ላይ አፈሰሰ ማለት፡- ፍትሐእግዚአብሔር ተደረገ ማለት ነው፡፡

**ምዕራፍ 17**

**ምዕራñ አስራ ስምንት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፡-**

1. በብዙ ውኃ ላይ የተቀመጠች ዘማ የተባለች፡- ባቢሎን ናት ቤተአይሁድ ሮም ብለው የተረጐሙ መምህራንም አሉ፡፡
2. የስድብ ስም የተሞላበት ቀይ አውሬ የተባለ፡- ሐሳዌመሲሕ ነው፡፡
3. አውሬው በገናንነት አለ፣ በገናንነት የለም ማለት፡- አለ የተባለ ከአዳም እስከክርስቶስ ሰው መሆን ድረስ ሲሆን የለም የተባለ ደግሞ ከክርስቶስ ሰው መሆን በኋላ ድል ተነስቶ ነው፡፡
4. ከከተማ ነግZ ይወጣል ማለት፡- በሐሳዌመሲሕ ጊዜ እንደገና መነሣቱን መናገር ነው፡፡
5. 7ቱ ነገሥታት፡- በየጊዜው የሚነሡትን በፍጹም ቆጥሮ ነው ሁለቱ መንግሥተሮም፣ መንግሥተ ተንባላት ናቸው፡፡

**ምዕራፍ 18**

**ምዕራñ ሃያ አራት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፡-**

1. የባቢሎን ጥፋት፡- ፈወስናሃ ለባቢሎን ወኢተፈወሰት ኤር. 51፡9
2. ጸኑዕ ስልጣን ያለው መልአክ የተባለ፡- ጌታ ነው
3. መዕራñ በአጠቃላይ የባቢሎን አወዳደቅ የሚናገር ነው

ምዕራፍ 19

ምዕራፅ ሃያ አንድ ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ

1. ወደሠርጉ ቤት እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው፦ ማለት ለክብር የበቁ ማለት ነው።
2. መልአኩ አትስገድልኝ ማለቱ፦
   - ዮሐንስ ከፍጹምነት መዓርግ ደርሶ ስለነበር ለትህትና ሲሆን
   - ዮሐንስ መልአኩ ጌታ መስሎት የባሕርይ ስግደት ሊሰግድለት ስለነበር ከለከለውና ሁላችንም ለእግዚአብሔር እንስገድ አለው።
3. አምባላይ ፈረስ ማለት፦ ንጹሀባሕርይ መሆኑን ያስረዳል።
4. ዐይኖቹ ነደዕሳት ናቸው ማለት፦ ትእምርተበቀል፣ ትእምርተ መዓት ገንዘቡ የሚሆን ማለት ነው።
5. ደም የተረጨ ልብስ ማለት፦ ለሰው ብሎ መሞቱን ያስረዳል።

ምዕራፍ 20

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አስራ አምስት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፦

1. ከሰማይ የወረደ መልአክ የተባለ፦ ጌታ ነው
2. ሽሕ ዘመን አጋዘው ሲል፦ ሽ ዘመን የተባለ ዘመነወንጌል ፣ የፍርድ ቀን፣ ከምጽአት በኋላ ያለው ዘመን ነው ተብሎ ተተርጉሟል።
3. ከክርስቶስ ጋር ሽ ዘመን ይነግሣሉ ማለት፦ አድሮባቸው ይኖራል ማለተ ነው። ሽ ዘመን እንደላይኛው ይተረጐማል።
4. ጎግ፣ ማጎግ ማለት፦ ብዙ የብዙ ብዙ ንጉሡን፣ ሠራዊቱን፣ አይሁድ ተንባላት መምለክያነጣዖት ተብሎ ተተርጉሟል።
5. መጽሐፈሕይወት ተገለጠች ማለት፦ መጽሐፈ ሕይወት የተባለች ወንጌል ናት ተገለጠች ማለት ወንጌል ዋጋ ማሰጠቷን መናገር ነው።

መዕራፍ 21

ይህ ምዕራፍ ሃያ ሰባት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ፦

1. አደስ ሰማይና አዲስ ምድር የተባለች፦ መንግሥተሰማያት ናት።
2. እንባን ከዓይናቸው የርቃል ማለት፦ ዋጋቸውን ሰጥቶ ደስ ያሰኛቸዋል
3. ከሕይወት ውኃ መንጭ ይጠጣ ዘንድ እሰጠዋልሁ ማለት፦ በልጅነት የሚሰጥ ክብር የክብር ክብር እሰጠዋለሁ ማለት ነው።

4. አስራ ሁለቱ የከበሩ ድንጋዮች /አዕናቁ/ የ12ቱ ነገደ እስራኤል ምሳሌዎች ሲሆኑ 12ቱ ነገድ ደግሞ የ12ቱ ሐዋርያት ምሳሌዎች ናቸው፡፡
   - ኢያሰጲድ የሮቤል የጴጥሮስ
   - ሰንፔር ስምዖን እንድርያስ
   - ኬልቄዶን ይሳኮር ማቴወስ
   - መረግድ ይሁዳ ዮሐንስ
   - ሰርዶንክስ ሌዊ የዕቆብ ወ/ዘብዴዎስ
   - ሰርጽዮን ጋድ ያዕቆብ ወ/እልፍዮስ
   - ክርቲሎቤ ንፍታሌም በርተሎሜዎስ
   - ቢረሌ ዛብሎን ፊልጶስ
   - ወራውሬ ብንያም ናትናኤል
   - ክርስጵራስስ አሴር ቶማስ
   - ያክንት ዮሴፍ ታዴዎስ
   - አሜቴስጢኖስ ዳን ማትያስ

ዮሐንስ በራእዩ መንግሥተሰማያትን በ12ቱ አዕናቁ ተሰርታ አጊጣ ማየቱ ነቢያት፣ ሐዋርያት አንድ ሁነው መንግሥተ ሰማይ የመግባታቸው ምሳሌ ነው፡፡

## ምዕራፍ 22

### ምዕራፍ አሰራ ስምንት ቁጥሮች ሲኖሩት በውስጡ

1. የሕይወት ውኃ የሚፈስበት ወንዝ ማለት፡- በልጅነት ክብር የሚሰጥበት ማለት ነው፡፡
2. ዕፀ ሕይወት ማለት፡- ሥጋው ደሙ፣ ቃለ እግዚአብሔር፣ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መስቀል፣ መንግሠተሰማይ ተብሎ ተተርጉሟል፡፡
3. ልብሳቸውን ያጠቡ ሰዎች ንዑዳን፣ ክቡራን ናቸው ማለት፡- ሰውነታቸውን ከኃጢአት የለዩ ማለት ነው፡፡
4. 5ቱ ከለባት/ውሾች/ የተባሉ፡- አስማተኞች፣ ዘማውያን፣ ቀታልየን/ ነፍሰገዳዮች/ ጣዖት አምላኪዎች፣ ሐሰተኞች ናቸው፡፡

## ትክክለኛው መልስ ምረጥ

1.ከሚከተሉት አንድ ምዕራፍ ብቻ ያለው መልእክት የጻፈ ሐዋርያ ማን ይባላል?

ሀ. ቅ/ጴጥሮስ ለ. ቅ/ዮሐንስ ሐ ቅ/ይሁዳ መ. ቅ/ ያዕቆብ

2.ሦስት መልእክታት ያሉት ሐዋርያ ማን ይባላል

ሀ. ቅ/ያዕቆብ ለ. ይሁዳ ሐ. ዮሐንሰ መ. ጳጥሮስ

3.የቅ/ጴጥሮስ ትልዱ ነገዱ ከ -------------------ነው?

ሀ. ከነገደ ሮቤል ለ. ከነገደ ይሁዳ ሐ.ከነገደሌዊ

4.ቅ/ጴጥሮስን ያስገደለው ቄሣር-------------------- ይባላል

ሀ. ኔሮን ቄሣር ለ. ጢባርዮስ ቄሣር ሐ. አውግስጦስ ቄሣር

5. ከ4ቱ አፍላጋት በፈለገኤፍራጥስ የሚመሰል ወንጌላዊ /ሐዋርያ /ማን ይባላል?

ሀ. ቅ/ሉቃስ ለ. ቅ/ዮሐንስ ሐ. ቅ/ማቴዎስ መ. ሁሉም

6. የጌታን ስነስቅለት ለመጀመሪያ ጊዜ ከለሜዳ አስታጥቆ የሳለ ወንጌላዊ /ሐዋርያ/ ------ይባላል

ሀ. ቅ/ሉቃስ ለ. ቅ/ዮሐንስ ሐ. ሀናለ መ. መ/የለም

7. የወንጌላዊ ዮሐንስ በዓለዕረፍት /የተሰወረበት/ ቀን መቸ ነው?

ሀ. ጥቅምት 4 ለ.ታሀሳስ 4 ሐ.ጥር4 መ. ሁሉም

8. ወንጌላዊ ዮሐንሰ መልእክቱን የጻፈላት ሴት ማን ትባላለች?

ሀ. አውዶክሰያ ለ. ሮምና ሐ. ኤልዛቤል መ. መልስ የለም

9. ከወንጌላዊ ዮሐንሰ ጋር ብዙ መከራ በመቀበል ከሱ ጋራ የሴት አገልጋይ እስከመሆን ደርሶ የነበረ የዩሐንስ ደቀመዝሙር ማን ይባላል ?

ሀ.ፋጊር ለ. አብሮኩሮሰ ሐ. ያዕቆብ መ. ሁሉም

10.የያዕቆብ እኑሁ ለእግዚእነ በዓለዕረፍቱ መቸ ነው?

ሀ. ሰኔ 18 ለ .ሐምሌ 18 ሐ.ጥር 18 መ.መልስ የለም

## ማብራሪያ ስጥ

1. ሐዋርያው ያዕቆብ እኁሁ ለእግዚአነየጌታወንድም የተባለበት ምክንያቱ ምንድን ነው?የተባለበት ምክንያቱ ምንድን ነው---------
2. የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ እናትና አባት ማን ማን ይባላሉ
3. ራእየዮሐንሰን የጻፈው ማነው ? ወንጌላዊ ዮሐንስ ወይስዮሐንስ አፈወርቅ ?
4. 7ቱ አርእስተኃጣውዕ የሚባሉ ማን ማን ናቸው ?
5. 5ቱ ከለባት /ውሾች/ የተባሉ እነማን ናቸው፡፡ ዘርዝር